# እንግዶች ነን

አሸናፊ ተስፋዬ

ጥር  2016 ( 2024) ዓ.ም

# ማውጫ

ምስጋና.................................................................3

መቅድም...............................................................4

መግቢያ...............................................................8

የቃሉን ምንነት መረዳት.........................................12

የእንግድነት ኑሮ መሠረታዊያን...............................21

ሁለቱ መታረቅ የሚገባቸው ፅንፎች........................47

የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት በህይወታችን..............54

እጅ ከምን.........................................................67

ከመሄዳችን በፊት አንድ ናፍቆት..........................81

# ምስጋና

በመጀመሪያ ታናሹንና ደካማውን እኔን የማይገባኝን ምህረት እና ፀጋ እያበዛ በንስር ክንፍ የተሸከመኝን ዘላለማዊ አምላክ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ። በመቀጠል የቦሌ ቡልቡላ ቃለ-ህይወት ቤተክርስቲያን ዋና መጋቢ እሸቴ ይህን መጽሐፍ መፅሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ ዕይታ እንዳቀርብ ጊዜያቸውን እና ይሁንታቸውን በመስጠት ስላበረታቱኝ ምስጋና አቀርባለሁ ። በብዙ መንገድ የረዳችሁኝን ሁሉ ጌታ ኢየሱስ ዘመናችሁን ይባርክ ።

# መቅድም

የዛሬ ሁለት አመት አካባቢ ህይወቴ አስቤውና ገምቼ በማላውቀው ሁኔታ አዲስ ማርሽ ቅየራ ውስጥ ሲገባ እና ህይወት ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ምን እንደሚመስል እውነተኛ በሆነ መዳሰስ እና መነካካት መኖር ስጀምር በውስጤ ከተቀመጡ ትላልቅ ራዕዮች ውስጥ አንዱ መፅሐፍ ፅፎ ብዙዎችን መድረስ ነበር።

ከዛም አንድ መድረክ ላይ ወደፊት ምን ማድረግ ትፈልጋለህ ተብዬ ስጠየቅ የአፍ ወለምታ በሚመስል አጋጣሚ መፅሐፍ እፅፋለሁ ብዬ መለስኩ። ከመድረክ ከወረድኩ በኃላ ግን እራሴ ላይ የወቀሳ ዱላ ያነሳውት እራሴው ነበርኩ ። ምን ነክቶኝ ነው ይህ ሁሉ ሰው በተሰበሰበበት እንዲህ ያልኩት ፣ ባልፅፍ አሁን የሰማኝ ሰው እኔን ሲያስብ ምን ሊያስብ ይችላል በሚል የተጠራጣሪነት እና አለማመን ሀሳብ ብዙ ተብሰለሰልኩ። ግን ለካ አሸናፊ ሳይሆን ጌታ በውስጤ ይህን አይነት መፈለግ እንዳስቀመጠ እየተረዳው መጣው ። እርሱ ቅዱሱ የቀጠረው እና ያቀደው ወቅት ይህ ነበር። እውነት ነው ! አንዳንድ ነገሮቻችን የሚሰሩት ሳይገባን እና ሳንረዳው ነው። እኔንም ይህን ጊዜ አስቦ በቃሉ እያስታጠቀኝ ፣ በብዙ ዩኒቨርስቲ እና ቤተክርስቲያን በማውቃቸው ክርስቲያን ጓደኞቼ እና ወዳጆቼ እየመከረኝ ቀድሞ ውስጤ ላይ መፃፍ ጀምሮ ነበር። የዩኒቨርስቲ የአመት ቆይታ ጨርሼ ለአንድ ወር እረፍት ወደ ቤተሰብ ስመጣ ባለኝ አንድ ወር ከጌታ ጋር ያለኝን ህብረት ማጠንከር እና ትምህርቴን በተወሰነም ቢሆን ማጥናት የሚሉ ሁለት ዕቅዶችን ይዤ ነበር።

ነገር ግን በተፈጠረው የፀጥታ ሁኔታ ምክንያት ላልተወሰነ ጊዜ ቤተሰብ ጋር እንደምንቆይ ተነገረን። መቀየር የማንችለው ነገር እንደሆነ ተረዳው ፤ ግን ደግሞ " blessing in the disguise" ( በእርግማን ውስጥ ያለ ምርቃት ) እንደሚባለው ይህን መጥፎ የሚመስል አጋጣሚ የጌታን ፊት ለመፈለግ መጠቀም እንዳለብኝ ወሰንኩ። እግዚአብሔር እኛ ባሰመርነው ብቻ የሚሰራ አምላክ ባለመሆኑ አህያ

ሊፈልግ የሄደውን የቂስ ልጅ ሳዖል ከዕቅዱ ውጪ የሆነ የሰማይ አጀንዳ በሳሙኤል ተገናኘው። ይህ የሰማይ አጀንዳ ከመንደር አስተሳሰብ የሚያስወጣ እና ታሪክን ቀያሪ ነበር ፤ የሆነ ሰሞን ሞቅታ ያልሆነ እውነተኛ ለውጥ ነበር። ተረከዝ ይዞ የተወለደው ፤ ከታላቁ ይልቅ ኃያል ህዝብ እንደሚሆን ዕጣ የወጣለት ፤ አታላይነት ማንነቱ ነው እስኪባል የወረሰው ፤ የወንድሙን ብኩርና በምስር ወጥ አታሎ የወሰደው ፤ የዕድሜውን ሀያ አመት በአጎቱ ቤት የፈጀው ፤ ከእውነተኛ በረከት ጋር መገናኘት አንገብጋቢ የልቡ ጩኸት የሆነበት ያዕቆብ ባላሰው እና ባልገመተው አንድ ምሽት ሰማይ እና እርሱ ተገናኙ። የብዙዎች አባት ሊሆን ስሙ እስራኤል ተብሎ ተቀየረ ፤ አታላዩ ሰው ለአምላኩ በመሸነፍ ከእውነተኛ ባራኪው ጋር ጵንኤል ላይ ተገናኘ። በገማልያ እግር ስር ቁጭ ብሎ ህግን ሲማር እና ሲጠጣ የነበረው ፤ ከብንያም ወገን የሆነ ፈሪሳዊ ፤ ሀይማኖት በወለደው ቅንዓት ቤተክርስቲያንን አሳዳጅ የነበረው ሳዖል እንደለመደው ቅዱሳንን ሊያሳድድ እና ሊያስር በደማስቆ መንገድ እየተመመ በነበረበት ወቅት እያሳደደው የነበረውን ጌታ በሰማይ ብርሀን ተገኘ። አለኝ የሚለውን መመኪያ ሁሉ አስጥሎ ፤ ሀይማኖት የመረገበትን ቅርፊት ከአይኑ ገፍፎ ፤ ስለ ወንጌል ሁሉን የሆነ እና የአህዛብ ሐዋርያ አደረገው። ይብዛም ይነስ ሁላችን የራሳችን ደማስቆ አለን። ይህ የብዙዎቻችን የመነካት ታሪክ ነው።

ከሆነ ቆይታ በኃላ ግን ስለህይወት ማሰብ ጀመርኩ ፣ ለካ ትምህርት አይደለም የእኛ መዳረሻ ወይም ኖሮ ኖሮ መሞት ብቻ አይደለም ። እዚህ ምድር ላይ እንግዳ ነን። ይህን ማሰብ ስጀምር ተስፋ አስቆራጭ እና ጨለማ የሚመስለው አየር በብዙ ተስፋ እና ደስታ ተተካ። እኛ ለስራ ምድር ላይ ተቀመጥን እንጂ ሀገራችን በሰማይ ነው። ተስፋችን በዚህ ምድር ቆይታ ብቻ የተገደበ ሳይሆን ብል የማይበላው ፣ ዝገት የማያጠፋው ፣ ሌባ የማይሰርቀው መዝገብ በሰማይ አለን። ስለዚህ በእንግድነታችን ዘመን ለዚህ መዝገብ መስራት እንዳለብን ተረዳሁ ። የሰማይ መዝገብ ላይ ማጠራቀም ዘላለማዊ ክብርን የሚያቀዳጅ እንደሆነ መፅሐፍ ቅዱሳችን በብዙ መልኩ ያስረዳናል። እንደ ክርስቲያን መታወቂያችን ይህ መሆን እንዳለበት አምናለሁ። የጌታ ደቀመዝሙር የሆነን ከሌላው የሚለየው የበራለት ብርሀን ለሰማይ መዝገብ እንዲኖር የሚያደርግ ነው። በጌታ ሆኖ ከዚህ የተለየ የህይወት አቋም መያዝ ይቻላል ፣ የክርስቲያን የምድር ተልዕኮን ዘንግቶ እና ወደጎን ወርውሮ መኖር ይቻላል። ለዛም ነው “ደቀመዝሙር” የሚለውን አጠራር የተጠቀምኩት። ደቀመዝሙር የመምህሩ ፈለግ ተከታይ ነው። መምህሩን ለመምሰል የመምህሩን የህይወት አሻራ የሚከተል። ደቀመዝሙር ከመምህሩ

የሚቀበለው ከዓለም የተለየ የህይወት አቋም አለው። ጌታ ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 6 ላይ ለደቀመዛሙርቱ የተለየ የህይወት መመሪያ ( principle ) ሲሰጣቸው እንመለከታለን። አይሁድ እና አህዛብ ዘንድ ከሚታወቀው የህይወት ምልልስ የተለየ ከኢየሱስ ህይወት የተቀዳ የኑሮ ዘይቤን ይሰጣቸዋል። ይህ የህይወት ዘይቤ ደግሞ የሰማይን መዝገብ ማዕከል ያደረገ ነው። የእግዚአብሔር መንግስት የሚፈልገው አኗኗር ነው የሰማይ መዝገብ ማለት። ብዙ የአዲስ ኪዳን መልዕክታት ወደላይ ጠቋሚዎች ናቸው። የእግዚአብሔር መንግስት ስለሚታየው ምድራዊ ቁስ እንዲሁም መብልና መጠጥ እንዳልሆነ አስምረው ይናገራሉ።

በዚህ ወቅት አንዳንዶች ተስፋ ሲቆርጡ ፣ ሌሎች ራሳቸውን ሲያጠፉ እና ህይወት እጅግ መራራ የሆነችባቸው ብዙዎችን ሳይ እራሴንም የጠየኩበት ጉዳይ ሆነ። ትንሽ ከተረዳውት ለምን ክርስቲያናዊ የምድር ቆይታ ምን መምሰል እንዳለበት መፅሐፍ አልፅፍም የሚል ሀሳብ ልቤ ውስጥ እረፍት ነሺ እና አንገብጋቢ ሆኖ ተቀመጠ። በዚህ ጉዳይ በጌታ ፊት በፀሎት ከሆንኩ በኃላ ለመፃፍ ተነሳሁ። ምናልባት እዚህ መፅሐፍ ውስጥ ለክርስትና ህይወትዎ ስንቅ የሚሆን መልካም ነገር ካገኙ ክብሩን ሁሉ እግዚአብሔር ይውሰድ ፤ እኔ የእርሱ መጠቀሚያ ባሪያ ብቻ ነኝ። መልካም ንባብ !!

# መግቢያ

ይህ ርዕሰ ጉዳይ በክርስቲያኖች ዘንድ ዋና የህይወት ማዕከል የሆነ ፥ አሁን ባለንበት ዘመን ግን ከብዙ ክርስቲያኖች አዕምሮ ውስጥ የሸሸ እንዲሁም በምስባኮቻችን ላይ የስብከት ርዕስ ሆኖ የማይታይ ነው። በእርግጥ በተቃራኒው የክርስትና መስመር ላይ ይህን ርዕሰ ጉዳይ የሚያስተምሩ ፣ የሚናገሩ የሉም ማለት አይቻልም ። ይህን መጽሐፍ የምናነብ ብዙዎቻችን “ መጻተኛ” እና “እንግዳ” በሚል ጉዳይ መሠረት ያደረጉ በቁጥር በዛ ያሉ መጽሐፍት አንብበን ላይሆን ይችላል ።

ግን ሊቀየር የማይችለው ቋሚ ሀቅ እና እውነት እናንተ ክቡራን አንባቢያን ፡ እኔም በዚህች እያረጀች ባለች ምድር “መጻተኞች” እና “ እንግዶች” መሆናችን ነው። እንደውም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥሪያችን በዋናነት ይህ ነው። ምናልባት ይህን ሐሳብ ስናነብ ከግል ህይመታችን ጋር እያገናኘን ብዙ ስሌት ውስጥ እየገባን ሊሆን ይችላል። ይህ ከእኔ ህይወት ጋር ምን ያገናኘዋል ? አሁን ለምማረው ትምህርት ምን ይጨምራል ? ከምሰራው ስራ ጋር በምን ሊገናኝ ይችላል ?? እያልን በእነዚህ እና በሌሎችም ጥያቄዎች እየተብሰለሰልን ሊሆን ይችላል ። መጠየቅ በራሱ ክፋት ባልነበረው ፥ ግን ደግሞ በእርግጥም አስበንበት ወደዚህ አይነት ስሌት ( calculation) ገብተን ከሆነ ተስፋችን ምድራዊ ነው ማለት ነው። ሰማይ ከህይወታችን እና ከሀሳባችን እርቋል ማለት ነው። የዳንበትን ትልቁን ምክንያት ማለትም የሰማይን ርስት ወደሚቀጥለው መቶ አመት ወይም ሚሊንየም እያዛወርን እና እያስተላለፍን ነው ማለት ነው። እግዚአብሔርን ራሱን ሳይሆን የእጆቹን ብቻ ፈላጊዎች እና ቃራሚዎች ነን ማለት ነው ። ለዚህ ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ እቅጩን ይመልሳል ;

"በዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ፥ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን።"

**— 1ኛ ቆሮንቶስ 15፥19**

እግዚአብሔር አምላክ ርስት አድርጎ የተቤዠውን ህዝቡን በደንብ እንደሚባርክ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል ። በእውነት እና በቅድስና የሚኖሩ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር በረከት ተካፋዮች ናቸው። በማቴዎስ 6 የመጨረሻ ቁጥሮች ላይ ጌታችን ኢየሱስ አስቀድመን መንግስቱንና ፅድቁን እንድንፈልግ ተናግሮ ሌላው ለህይወት የሚያስፈልገን ሁሉ እንደሚጨመር አክሎበታል። በእግዚአብሔር መንግስት ቅኝት ውስጥ ኑሯቸውን የቃኙ አማኞች ከእግዚአብሔር በረከት አይጎድሉም። ግን ደግሞ እግዚአብሔር ሲባርክ ትልቁ ምስል እንዲረሳ እና እንዲዘነጋ ፍላጎቱ አይደለም። በእነዚህ በረከት ውስጥ አልፈው ትልቁን የእግዚአብሔርን በረከት ጌታችን እና መድህኒታችን ኢየሱስን ካላገኙት በእርግጥም የእግዚአብሔርን ሀሳብ ስተዋል። ማስቲካን ያጠግበኛል ብሎ የሚገዛ ሰው ያለ አይመስለኝም ፤ ማስቲካ ገዝቶ ወዲያው የሚውጥ ሰው ምንኛ የዋህ ነው: የማስቲካ ዋና ዓላማ በማኘክ ውስጥ ያለውን ጣዕም እና ደስታ መስጠት ነው። ጣዕሙን ሳያጣጥም ደጋግሞ ሳያኝክ እንደገዛ የሚበላ ሰው የማስቲካን በረከት ማጣት ብቻ ሳይሆን ማስቲካ ወደ ውስጠኛው የሰውነታችን ክፍል በመግባቱ ያለው ተያያዥ የጤና ችግር ተጠቂ ይሆናል ። የእግዚአብሔር ሐሳብ እና በረከትም ከዚህ የተለየ አይመስለኝም ። እግዚአብሔር በበረከት ውስጥ እጁን ዘርግቶ እኛን ከሚወደው ፣ አንደያ ከሆነው ልጁ ጋር ማጨባበጥ ነው። ምክንያቱ ደግሞ እግዚአብሔር አብን ያስደሰተ ብቸኛ ኢየሱስ በመሆኑ አብ ደስ በተሰኘበት አስቀድመን ካልረካን እና የደስታን ጣሪያ ካልነካን በምንም መደሰት አንችልም ። ሰው በኢየሱስ ካልተደሰተ በቆርቆሮ እና በወረቀት ሀብት ፈፅሞ መደሰት አይችልም ። እስኪ ፊልጶስ ሰማርያ በነበረው አገልግሎት ምን እንደተከናወነ እንመልከት ;

**ሐዋርያት 8**

**[5] ፊልጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው። …**

**[8] በዚያችም ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ።**

በታላቅ ስደት ውስጥ እያለፈች በነበረችው የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ሁሉ ወደተለያየ ስፍራ በተበተኑበት ወቅት ፊልጶስ ሰማርያ ላይ ክርስቶስን ብቻ ሰበከ። ሐዋርያት ክርስቶስን መስበክ ምን ማለት ነው ብለን ብንጠይቃቸው;

**"እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ ለአሕዛብም ሞኝነት ነው፥"**

**— 1ኛ ቆሮንቶስ 1፥23**

**"ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታ እንደ ሆነ እንጂ ራሳችንን አንሰብክምና፥ ስለ ኢየሱስም ራሳችንን ለእናንተ ባሪያዎች እናደርጋለን።"**

**— 2ኛ ቆሮ 4፥5**

የሰማርያ ደስታ ምክንያት ኢየሱስ ብቻ ነበር። የሐዋርያቱ ንግግር እና ስብከት የኢየሱስ ጌትነት ብቻ ነበር። በሐዋርያት እና ነቢያት መሠረት ላይ መታነፃችንን እንደ ቤተክርስያንም ሆነ እንደ ግለሰብ እርግጠኛ መሆን ይገባናል።

**"በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ።"**

**— ኤፌሶን 2፥22**

ይህ መሠረት ሽራርፎ መቀጠል እና አዲስ መገለጥ የማያስፈልገው ጌታችን ኢየሱስ አንዴ የመሠረተው ነው። ማንም ሌላ ይመሰረትበት ዘንድ የተገባ አይደለም። መሠረቱ የክርስቶስ ትምህርት ( Doctrine of Christ ) ነው። ይህ ትምህርት ደግሞ አንድን አካል ብቻ የሚያጎላ እና የሚያሳይ ነው። እርሱም ከሰማያተ ሰማይ ወርዶ በግርግም የተወለደ ፣ የመስቀልን ሞት የሞተ ፣ ሲኦልን

ድል የነሳ እና የሞትን መውጊያ ሰብሮ ከሙታን በኩር የሆነው ፤ ወደ አባቱ ቀኝ ያረገ ፤ ተመልሶ በንጉስ የክብር አመጣጥ የሚመጣው የእግዚአብሔር ልጅ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

**“ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፥ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።”**

**— 1ኛ ቆሮንቶስ 3፥11**

እርሱ አሁን የጀመርነውን እምነት ጀማሪ ደግሞም በዳግም ምፅዓቱ ይህን እምነት የሚፈፅምልን ነው። ይሄ ነው የተደላደልንበት መሠረት። ከዚህ ውጪ ያለው መሠረት ሌላ ቤት የመገንባት ጥረት ይሆናል ፤ ይህ ደግሞ ተሰርቶ ሲያልቅ ኢየሱስን ጌታ አድርጎ የሚያኖር ሳይሆን ሌላ አዲስ ጌታ የሚሾም ነው። ምድር ላይ የቆይታ ዘመን በተበጀልን የእንግድነት ዘመናችን ትልቁ መያዝ የሚገባን መፅሐፍ ቅዱሳዊ እውነት በእግዚአብሔር ዘላለማዊ የድነት ዕቅድን ያማከለ ኑሮን መኖር ጥሪያችን መሆኑን ነው።

# የቃሉን ምንነት መረዳት

የቃሉን ትክክለኛ ትርጓሜ መረዳት የሙሉ መፅሐፉን ሀሳብ በትክክል ለመረዳት ጠቃሚ ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን እንደ መልካም እሴት ከሚነገሩልን ነገሮች አንዱ እንግዳ ተቀባይነታችን (hospitality) ነው ፤ በእርግጥ አሁን ላይ ይሄ ገፅታ እንደድሮው ጎልቶ እየታየ ላይሆን ይችላል የሚለው ብዙዎች የገዙት አስተሳሰብ ነው።

ታዲያ ቤታችን ከመጣው እንግዳ የምንወስዳቸው እሳቤዎች አሉ። እንግዳ ሂያጅ መሆኑን በደንብ እናውቃለን ። ያለን እንክብካቤ እንኳን ይህን ታሳቢ ያደረገ ነው። ብዙ ጊዜ እንደማይቆይ እና ልቡ እየሄደ ያለበት መዳረሻ ጋር እንደሆነ ስለምናውቅ እንዳይከፋው ፣ ብቸኝነት እንዳይሰማው ፣ እንዳይራብ በብዙ እንክብካቤ እንመግበዋለን። ይህን የምናደርገው አንድም ከመልካምነት ተነስተን ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ እንግዳው ተሰናብቶን ሲሄድ ስለእኛ መልካም ስም ይዞ እንዲሄድ ነው።

ይሄ የእንግዳ ተቀባዩ ድርሻ ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ እንግዳው የሚይዛቸው የእግድነት ባህሪያት አሉት። የትኛውም እንግዳ በእንግድነት ሲቀመጥ ብዙ ምቾት እና ድሎት ፈላጊ አይደለም ። ምክንያቱም ቋሚ መኖሪያው እና የመጨረሻ የጉዞው ማብቂያ አድራሻቸው ካልሆነ ስፍራ የተለየ ነገር አይጠብቅም ። ብቻ ጊዜያዊ ምግብ እና መጠለያ ካገኘ በቂው እንደሆነ ይገነዘባል ። ለተወሰነ ጊዜ በሚኖረው እንግድነት ያረፈበትን ቤት ህግ ሳይጥስ በመልካም ባህሪ ምሳሌ ለመሆን የተቻለውን ያደርጋል።

ነገር ግን ሁሉን ነገር ይቀበላል ማለት አይደለም ። ከእርሱ አስተሳሰብ ፣ ልማድ ፣ የአኗኗር ዘይቤ ጋር የማይስማሙ እና አብረው ሊሄዱ የማይችሉ ሁኔታዎች ላይ ግልፅ የሆነ አቋም እና ድንበር አለው። እኔን አይመጥንም ብሎ ያሰበው ቀልድ እና ወሬ ሲወራ እንኳን እነሱን በማያስቀይም መልኩ ፈቀቅ ብሎ የራሱን ነገር ወደማድረግ ይሄዳል ። ከሚያምነው እምነት ጋር የሚጋጭ ድርጊት ለማድረግ ፈቃደኛ አይደለም ፤ ምክንያቱም እንግዳ ነውና። ይህን ሁሉ ያልኩት ወደ እኛ የክርስትና እንግድነት ህይወት ለመምጣት መንደርደሪያ እንዲሆነን ነው። “እንግዳ”

የሚለው የቃል አገላለፅ ማህበረሰባዊ አረዳዱን በዚህ መልኩ ከተረዳን በቀጣይነት የመፅሐፉም ሀሳብ ወደሆነው መፅሐፍ ቅዱሳዊ ምልከታን እንመልከት ።

መፅሐፍ ቅዱሳችን ላይ በሁለት የተለያያ መልክ ፤ ተመሳሳይ የባህሪ መላበስን ይዞ እናገኛለን ። የመጀመሪያው የቃሉ አረዳድ የአንድ ወገን ወይም ማህበረሰብ አባል እና አካል አለመሆንን የሚያሳይ ነው። በተለይ በብሉይ ኪዳን በብዙ የሚታይ ነበር። የአንድ ህዝብ ወይም ማህበረሰብ ወገን ያልሆነ “እንግዳ” ወይም “መፃተኛ” ተብሎ ይቆጠራል ። ከአብርሃም መጠራት ጀምሮ እስራኤል እንደ ህዝብ እንግዳ እና መፃተኛ ሆነው ቆይተዋል። አብርሃም ከቤተሰቡ እና ከወገኑ ጋር በዑር ምድር ተቀምጦ እግዚአብሔር ጠርቶት በእንግድነት ወደሚቀመጥበት ሀገር አወጣው። የእግዚአብሔር ዘላለማዊ አጀንዳ በአብርሃም ጀመረ። እግዚአብሔርም አብርሃምን በተለያየ ጊዜያት የእንግድነት ኑሮን ያስኖረው ነበር።

***“በምድርም ራብ ሆነ፤ አብራምም በዚያ በእንግድነት ይቀመጥ ዘንድ ወደ ግብፅ ወረደ፥ በምድር ራብ ጸንቶ ነበርና።”***
***— ዘፍጥረት 12፥10***

***“በእንግድነት የምትኖርባትን ምድር፥ የከነዓን ምድር ሁሉ፥ ለዘላለም ግዛት ይሆንህ ዘንድ ለአንተና ከአንተ በኋላ ለዘርህ እሰጣለሁ አምላክም እሆናቸዋለሁ።”***
***— ዘፍጥረት 17፥8***

***“እነርሱም፦ ወዲያ ሂድ አሉት። ደግሞም እንዲህ አሉ፦ ይህ ሰው በእንግድነት ለመኖር መጣ፥ ፍርዱንም ይፈርድ ዘንድ ይፈልጋል፤ አሁን በአንተ ከእነርሱ ይልቅ ክፉ እናደርግብሃለን። ሎጥንም እጅግ ተጋፉት፥ የደጁንም መዝጊያ ለመስበር ቀረቡ።”***
***— ዘፍጥረት 19፥9***

***“አብርሃምም ከዚያ ተነሥቶ ወደ አዜብ ምድር ሄደ፥ በቃዴስና በሱር መካከልም ተቀመጠ በጌራራም በእንግድነት ተቀመጠ።”***
***— ዘፍጥረት 20፥1***

እነዚህ ሁሉ የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እግዚአብሔር ለአብርሃም ሊገልጠው ያለው የሰማይ መኖሪያ እንዳለ እና ይህም በጨረፍታ ተስፋ እንዲያደርግ አድርጎታል።

***"መሠረት ያላትን፥ እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ይጠብቅ ነበርና።"***

***— ዕብራውያን 11፥10***

ይስሀቅ እና ያዕቆብም የዚህ ፈለግ ተከታዮች ነበሩ።

***ያዕቆብም ወደ አባቱ ወደ ይስሐቅ አብርሃምና ይስሐቅ እንግዶች ሆነው ወደ ተቀመጡባት ወደ መምሬ ወደ ቂርያትአርባቅ እርስዋም ኬብሮን ወደምትባለው መጣ።"***

***— ዘፍጥረት 35፥27***

የዕብራውያን ፀሐፊ ስለነዚህ የእምነት አባቶች ምዕራፍ 11 ላይ በግልጥ ተናግሯል ።

***"እነዚህ ሁሉ አምነው ሞቱ፥ የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል አላገኙምና፤ ዳሩ ግን ከሩቅ ሆነው አዩትና ተሳለሙት፥ በምድሪቱም እንግዶችና መጻተኞች እንዲሆኑ ታመኑ።"***

***— ዕብራውያን 11፥13***

ተስፋውን ሳያገኙት ተስፋ አድርጎው እና ታምነውበት አንቀላፍተዋል ። በአብርሃም መጠራት የጀመረው የእግዚአብሔር የምድር ቤተሰብ ታሪክ በይስሀቅ እና ያዕቆብ ቀጥሎ ሰባ የሚጠጉ የያዕቆብ ቤተሰብ ላይ ደረሰ። ፍፃሜን ከጅማሬው የሚያውቀው እግዚአብሔር አስቀድሞ ለወዳጁ አብርሃም እንደተናገረው ዮሴፍን ምክንያት አድርጎ የያዕቆብ ቤተሰብ ወደ ግብፅ እንዲወርዱ አደረገ።

**“አብራምንም አለው፦ ዘርህ ለእርሱ ባልሆነች ምድር ስደተኞች እንዲሆኑ በእርግጥ እወቅ፤ ባሪያዎች አድርገውም አራት መቶ ዓመት ያስጨንቋቸዋል።”**

**— ዘፍጥረት 15፥13**

**“ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ወገኔ በዚያ እንግዳ ሆኖ ይቀመጥ ዘንድ አስቀድሞ ወደ ግብጽ ወረደ፥ አሦርም ያለ ምክንያት በደለው።”**
**— ኢሳይያስ 52፥4**

ሰባ ሆኖ የገባው የያዕቆብ ቤተሰብ በግብፅ ሀገር ውስጥ በእንግድነት ይኖር ጀመር። አንዳች የእግዚአብሔር መለኮታዊ አጀንዳ እየተሰራ ነበር። የእግዚአብሔር ዘላለማዊ አጀንዳው የሰው ልጅ ያስወሰደውን ክብር ዳግም መመለስና ሰው እና መለኮት የነበራቸው ህብረት እንዲታደስ ነው። በዚህ ውስጥ ለጠራቸው ምርጦቹ የገባው የተስፋ ቃል እየተፈፀመ ነበር። አብርሃምን ዘርህን እንደ ምድር አሸዋ አደርጋለሁ ብሎ የገባለትን ኪዳን በባዕድ ሀገር መፈፀም ጀመረ። የእስራኤላውያን የእንግድነት ህይወት በግብፅ ሀገር የእስራኤላውያንን ህዝብ አብዝቷል።

**“የእስራኤልም ልጆች አፈሩ፥ እጅግም በዙ፥ ተባዙም፥ እጅግም ጸኑ፤ ምድሪቱም በእነርሱ ሞላች።”**

**— ዘጸአት 1፥7**

የእግዚአብሔር ዕቅድ እንከን የማይገኝለት እና እርማት የማያስፈልገው ፍፁም ፃድቅነቱን የሚያሳይ ነው። አብርሃም ሞቷል ብሎ የገባውን ኪዳን የማያጥፍ ታማኝ አምላክ ነው። ምንም እንኳን እስራኤላውያን የገቡበት የእንግድነት ህይወት መካከል የእግዚአብሔር ዕቅድ ባይገባቸውም አምላካቸው ግን ስራውን እየሰራ ነበር። ማንም የሚመርጠው ህይወት አይደለም የእስራኤል ልጆች ያሉበት የእንግድነት ህይወት ። ብዙ ጭቆና ፣ መከራ እና ስቃይ የበዛበት ነበር። የእግዚአብሔር ዕቅድ በራሱ ለእስራኤላውያን የመከራ ፅዋ መብዛት ምክንያት ነበር ማለት ይቻላል ። ምክንያቱም እስራኤላውያን ቁጥራቸው እየጨመረ በመጣ መጠን

እና በፍሬያቸው ምድሪቱን መሙላት በቀጠሉ ቁጥር በግብፃውያን ላይ ስጋት ስለሆነባቸው ጉልበታቸውን መበዝበዝ እና መከራቸውን ማብዛት ተያያዙ።

**ዘጸአት 1**

**----------**

**[9] እርሱም ሕዝቡን፦ እነሆ፥ የእስራኤል ልጆች ሕዝብ ከእኛ ይልቅ በዝተዋል በርትተውማል፤**

**[10] እንዳይበዙ፥ ሰልፍም በተነሳብን ጊዜ ጠላቶቻችንን አግዘው እንዳይወጉን ከምድሪቱም እንዳይወጡ፥ ኑ እንጠበብባቸው አለ።**

**[11] በብርቱ ሥራም ያስጨንቁአቸው ዘንድ ግብር አስገባሪዎችን ሾመባቸው፤ ለፈርዖንም ፊቶምንና ራምሴን ጽኑ ከተሞች አድርገው ሠሩ።**

እግዚአብሔር በዚህ ሁሉ የእስራኤላውያን መሪር ባርነት ውስጥ አንድ ሉዓላዊ ማንነቱን መግለጥ ፈልጓል። ይህ ሉዓላዊነት ለምን ተብሎ የማይጠየቅ የአምላክነቱ ባህርይ ነው። ግብፃውያን እግዚአብሔር ምን አይነት አምላክ እንደሆነ ከሚነገር ታሪክ ባለፈ በተግባር ማሳየት ወድዷል። በዚህ የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ባህርይ ምክንያት እስራኤላውያን ዋጋ ሊከፍሉ ይችላሉ ግን ለምን ተብሎ አይጠየቅም ። እንደውም የእግዚአብሔርን ታላቅነት እና ሉዓላዊነት ማሳያ ከሆኑት መካከል በህይወታችን ውስጥ እግዚአብሔር ለሚሰራቸው አንዳንድ ነገሮች መልስ ማግኘት አለመቻላችን ነው። እርሱ እንደ ወደደ የሚያደርግ ፃድቅ አምላክ ነው። መልካሙ ነገር የህይወታችን ነገሮች ሁሉ ተጠቃለው ለበጎ መሆናቸው ነው። ምንም እንኳን የህይወታችን መሀል ሜዳ ብዙ እንቆቅልሽ የበዛበት ቢሆንም ፍፃሜውን እግዚአብሔር ማሳመሩ ነው።

**“እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።”**

**— ሮሜ 8፥28**

እግዚአብሔር ለግብፃውያን በተለያዩ ድንቅ እና ተዓምራቶች ማንነቱን ገልጦ እስራኤላውያን ከባርነት አስወጣቸው። የእግዚአብሔር ርስት አድርጎ በመረጠው ህዝብ የጀመረው የእንግድነት ሀሳብ በብሉይ ኪዳን እንዲህ ባለ ሁኔታ በአበይት ክስተቶች ታጅቦ ቀጠለ። እስከ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋ መገለጥ እና የቤተክርስቲያን መመስረት ድረስ የእግዚአብሔር የእንግድነት ሀሳብ በግለሰቦች መቀጠል ጀመረ። በተለይም የእግዚአብሔር መንግስትን በምድራዊው ዙፋን ወካይ በተደረገው እና ንግስና ከዘርህ አይጠፋም በተባለው ዳዊት ቀጥሏል።

***“እኔ በምድር እንግዳ ነኝ፤ ትእዛዛትህን ከእኔ አትሰውር።”***
***— መዝሙር 119፥19***

***“በእንግድነቴ አገር ሥርዓትህ መዝሙር ሆነችኝ።”***
***— መዝሙር 119፥54***

ሌላው በስያሜ ተመሳሳይ የሆነ ግን ደግሞ በአገላለፅ እና በአረዳድ ለየት ያለው የእንግድነት ሀሳብ በተለይ ደግሞ በብሉይ ኪዳን የነበረው ከእስራኤላውያን ውጪ የነበሩት ህዝቦች የሚጠሩበት ስያሜ ነው። ከእስራኤል ወገን ውጪ የሆነ ህዝብ አህዛብ ተብሎ ይጠራ ነበር።

ቀጥሎ የቀረቡት የመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ይህንን ሀሳብ በጥሩ ሁኔታ የሚያንፀባርቁ ናቸው። እግዚአብሔር አንድን ህዝብ በሉዓላዊ ፈቃዱ በመምረጡ እርሱ በሰጠው ህግ እና የአኗኗር ዘይቤ ብቻ እንዲኖሩ ስለፈለገ ከምድር አህዛብ እራሳቸውን እንዲለዩ ትዕዛዙ ነበር።

***“ጌታውም፦ ከእስራኤል ወገን ወዳልሆነች ወደ እንግዳ ከተማ አንገባም፤ እኛ ወደ ጊብዓ እንለፍ አለው።”***
***— መሳፍንት 19፥12***

***“አሁንም ለአባቶቻችሁ አምላክ ለእግዚአብሔር ተናዘዙ፥ ደስ የሚያሰኘውንም አድርጉ፤ ከምድርም አሕዛብና ከእንግዶች ሴቶች ተለዩ አላቸው።”***

***— ዕዝራ 10፥11***

***“የእስራኤልም ዘር ከእንግዶች ሁሉ ራሳቸውን ለዩ፥ ቆመውም ኃጢአታቸውንና የአባቶቻቸውን ኃጢአት ተናዘዙ።”***
***— ነህምያ 9፥2***

ወደተቀደሰው የእስራኤል ጉባኤ ሌሎች ህዝቦች እንዲገቡ አይፈቀድም ነበር። የሚገቡም ከሆነ በህጉ የሚጠይቀውን ግርዘት ከፈፀሙ በኃላ ነው።

**ዘጸአት 12**

**----------**

**43 እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን አለ፦ ይህ የፋሲካ ሕግ ነው፤ ከእርሱ እንግዳ ሰው አይብላ።**

**…**

**45 መጻተኛና ሞያተኛ ግን ከእርሱ አይብሉ።**

***“እንግዳ ሰውም በመካከላችሁ ቢቀመጥ ለእግዚአብሔርም ፋሲካን ሊያደርግ ቢወድድ፥ አስቀድሞ ወንድ ሁሉ ይገረዝ፥ ከዚያም ወዲያ ይቅረብ ያድርግም፤ እንደ አገር ልጅም ይሆናል፤ ያልተገረዘ ሁሉ ግን ከእርሱ አይብላ።”***

***— ዘጸአት 12፥48***

ክህነትን ጠንቀቅ አድርጎ በሚገልጸው የዘሌዋውያን መፅሐፍ ውስጥ ግን እግዚአብሔር ይህን መራራቅ በተወሰነም ቢሆን ለማጥበብ በእስራኤላውያን ዘንድ የአስተሳሰብ አድማስ ማስፋትን አምጥቷል ። ነገር ግን ጥሪን መሰረት ያደረገ ሳይሆን ለእንግዳ መደረግ ካለበት ግብረገባዊ ባህርይ አንፃር ነበር።

**“እናንተ በግብፅ ምድር እንግዶች ነበራችሁና ከእናንተ ጋር የሚቀመጥ እንግዳ እንደ አገር ልጅ ይሁንላችሁ፥ እርሱንም እንደ ራስህ ውደድ፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ።”**

**— ዘሌዋውያን 19፥34**

የዚህ መፅሐፍ የእንግድነት ሀሳብም ከላይ አስቀድሞ የገለፀውን በአብርሀም የጀመረው ፣ እንደ ህዝብ በእስራኤል እና ከዚያ በኃላ ደግሞ እንደ ዳዊት ባሉ ግለሰቦች የቀጠለውን የእንግድነት ሀሳብ መሠረት ያደረገ ገው። በመለኮት ተፅዕኖ የተደረገበትን የእንግድነት ህይወት የሚዳስስ ነው። ዘላለማዊውን የእግዚአብሔርን ሀሳብ ያደረገውን የክርስቲያን የምድር ቆይታ የሚዳስስ ነው። ይህም የመንግስተ ሰማይ ተጓዥን የሚመለከት ነው።

በአጠቃላይ እንግዳ የሚለው ቃል ፍቺ ለመፅሐፍ ቅዱሳችን መሠረት በሆኑት ቋንቋዎች እና ሌሎችም በሚቀጥለው መልኩ ተቀምጧል ።

**እንግዳ** ፣ ከሌላ ወገን የመጣ ፣ ክርስቲያን በዚህ ዓለም

***መጻተኛ*** ፤ በሰው አገር የሚኖር ፥ እንግዳ ፥ መጤ

ግሪክ ፤ **proskynitis**

**Parepidemos** ( መጤ ነዋሪ ፣ እንግዳ )

ላቲን ፤ **peregrinus** ( ጊዜያዊ ነዋሪ ፣ በጉዞ ላይ ያለ ሰው፣

እንግዳ ፣ ከሌላ ስፍራ የመጣ )

**Thayer’s Greek Lexicon ፡**

1. **እንግዳ በሆነ ቦታ እየተጓዘ ያለ**
2. **በአዲስ ኪዳን ዘይቤያዊ ( metaphorically ) አገላለጽ የመንግሥት ሰማይ ተጓዥ**

# የእንግድነት ኑሮ መሠረታዊያን

## 1. እንደ መጻተኛ እና እንግዳ ለመኖር መያዝ የሚገባን አስተሳሰብ

**“ወዳጆች ሆይ፥ ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት ትርቁ ዘንድ እንግዶችና መጻተኞች እንደ መሆናችሁ እለምናችኋለሁ፤”**
**— 1ኛ ጴጥሮስ 2፥11**

ስለራሳችን ያለን ሀሳብ ይህ መሆን አለበት። ሰይጣን በሚገዛበት የዓለም ስርዓት ውስጥ እንግዶች እና መጻተኞች ነን። የእንግድነት ኑሯችን በጠላት ቀጠና ውስጥ መሆኑ ለአፍታ መዘናጋት እንደሌለብን ትልቅ ማሳመኛ ( conviction ) ነው። የማንነታችን መለኪያ ከዚህ ዓለም የሚኮረጅ ወይም የሚቀዳ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር ካለን ህብረት እንዲሁም ከህዝቡ ጋር ካለን ግንኙነት ከሰማይ አንፃር መሆን ይገባዋል።

ሐዋርያው ጴጥሮስ ይህን መልዕክት ሲፅፍ “ወዳጆች” ሆይ ብሎ ከላይ ያለውን ሀሳብ ያደርሳቸዋል። ይህ ደግሞ የእርሱን ሐዋርያዊ መውደድ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዲያስቡ የሚያደርግ ነው። ለእነዚህ ክርስቲያኖች ክርስትናን ትግል ብቻ የሚያደርግባቸው በታላቅ ፍቅር የመወደዳቸው ሚስጥር ነው። እዚሁ ምዕራፍ ላይ ቁጥር 2 ላይ “ ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደሆነ” ብሎ ወደዋናው ሀሳብ ይገባል። እንዴት ደስ የሚያሰኝ ነገር ነው !!! በመከራ ፣ በስደት በልዩ ልዩ ችግር ውስጥ የሚያልፍ ክርስቲያን እንዴት ባለ ታላቅ ፍቅር እንደተወደደ ሲገባው ተራራን ፈንቅል የሚያሰኝ እምነት እና በጌታ ያለ ድፍረት ይሰማዋል። የጳውሎስን መላ ሰውነትን የሚነዝር የህይወት መርህ ማየት በራሱ ክርስትናን እንድንወድ የሚያደርግ ነው።

**“ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ ወይስ ጭንቀት፥ ወይስ ስደት፥ ወይስ ራብ፥ ወይስ ራቁትነት፥ ወይስ ፍርሃት፥ ወይስ ሰይፍ ነውን?”**

**— ሮሜ 8፥35**

ጳውሎስ ሌላስ የተረዳከው መረዳት ምንድን ነው ሲሉት የሮሜ ቅዱሳን ;

**ሮሜ 8**

**38 ሞት ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን፥ መላእክትም ቢሆኑ፥ ግዛትም ቢሆን፥ ያለውም ቢሆን፥ የሚመጣውም ቢሆን፥ ኃይላትም ቢሆኑ፥**

**39 ከፍታም ቢሆን፥ ዝቅታም ቢሆን፥ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ።**

ከዚህ ሁሉ ነገር መውጫው ምንድን ነው ሲሉ የሮሜ ቅዱሳን አሁንም ይጠይቁታል, እንዲህ ይላቸዋል ;

**“በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።”**

**— ሮሜ 8፥37**

ይሄን እየፃፍኩ ምን እየተሰማኝ እንደሆነ ከማስረዳቹ እስኪ ራሳቹን የሮሜ ቅዱሳን ዘንድ አስቀምጣችሁ አስቡት። እግዚአብሔር በእርግጥም መልካም ነው። በልዩ ልዩ ችግር ውስጥ እያለፋቹ ያላቹ የአባቴ ብሩካን በዚህ መልዕክት መፅናናት ይሁንላችሁ ። አሜን !!

ተጓዥ የሆነ ሰው ሁልጊዜም የራሱ የሚሄድበት መንገድ አለው። ከዚህም በተጨማሪ በሚጓዝበት ስፍራ በቋሚነት ከሚኖር ሰው ይልቅ ስለህይወት የተለየ አረዳድ ወይም አስተሳሰብ አለው። እንደሌላው ባህል ፣ ወግና የህይወት መርህ አይኖርም ። ይህ ማለት ግን ሁሉን ስርዓት ተቃዋሚ እና ቸልተኛ ነው ማለት አይደለም ። እስኪ የሐዋርያው ጴጥሮስን መልዕክት እንመልከት ;

**“ስለ ጌታ ብላችሁ ለሰው ሥርዓት ሁሉ ተገዙ፤ ለንጉሥም ቢሆን፥ ከሁሉ በላይ ነውና፤”**

**— 1ኛ ጴጥሮስ 2፥13**

ስለጌታ ብለን በጊዜያዊነት የራሳችን የምናደርጋቸው (adopt) ስርዓቶች እና መርሆዎች ሊኖሩ ይችላሉ። በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አፈታት (hermeneutics) መሠረት ይህ ጥቅስ በአብዛኛው በቤተክርስቲያንና በሀገር ደረጃ ለተሾሙ የበላይ ባለስልጣናት መገዛትን ወይም ማክበርን የሚገልፅ ነው። ምናልባት ዘረኝነት እና ጎጠኝነት በነገሰባት ( ለወቅቱም ቢሆን ) ኢትዮጵያ ውስጥ ስለምንኖር መገዛት የሚለው ሀሳብ ላይመችን ወይም ሊጎረብጠን ይችላል። ነገር ግን ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ እና ቲቶ መልዕክቱ ያሰፈረውን እንመልከት ;

**"ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ። ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው።"**

**— ሮሜ 13፥1**

**"ለገዦችና ለባለ ሥልጣኖች የሚገዙና የሚታዘዙ፥ ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጁ፥ ማንንም የማይሰድቡ፥ የማይከራከሩ፥ ገሮች፥ ለሰው ሁሉ የዋህነትን ሁሉ የሚያሳዩ እንዲሆኑ አሳስባቸው።"**

**— ቲቶ 3፥1-2**

የሚገርመው ሁለቱንም በመልዕክቱ መደምደሚያ ላይ አፅንኦት ሰጥቶ ማሳሰቡ ጉዳዩ በእግዚአብሔር ዘንድ የመርህ ጉዳይ እንደሆነ ያሳያል ። ምክንያቱንም አብሮ አስፍሯል ።

**"ስለዚህ ባለ ሥልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሥርዓት ይቃወማል፤ የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ።"**

**— ሮሜ 13፥2**

መገዛት ስልጣን ላይ ከተቀመጠው ሰው ማንነት ጋር የተያያዘ ሳይሆን ከወንበሩ ጋር ( authority or position) የተያያዘ ነው። እንዴት የሚል ጥያቄ ከጫረብን ዳንኤል ከአንበሳ ጉድጓድ ከወጣ በኃላ ለንጉሱ ዳርዮስ ያሳየውን ክብር እንመልከት ;

**ዳንኤል 6**

**[21] ዳንኤልም ንጉሡን፦ ንጉሥ ሆይ፥ ሺህ ዓመት ንገሥ።**

**[22] በፊቱ ቅንነት ተገኝቶብኛልና፥ በአንተም ፊት ደግሞ፥ ንጉሥ ሆይ፥ አልበደልሁምና አምላኬ መልአኩን ልኮ የአንበሶችን አፍ ዘጋ፥ እነርሱም አልጐዱኝም አለው።**

ዳንኤል የሚያመልከውን አምላክ የሚያውቅ ሰው ስለነበር ከእግዚአብሔር አምላኩ ውጪ ሌላውን ወደውጭ በማለቱ የአንበሶች ጉድጓድ ተጣለ። ጉድጓድ ውስጥ ያስጣለው የዓለም ስርዓት ቢሆንም የዳርዮስ ስልጣን ከሰማይ የተሰጠ መሆኑ ስለገባው ትልቅ ትህትናን ለንጉሰ ሰጠ። ታዲያ ይህ የዳንኤል አክብሮት አምላኩን እግዚአብሔርን ያስከበረ አይመስላችሁም ?.

ሌሎች በግልጽ ያልተፃፉ ግን ደግሞ ለጌታ ብለን የምንታገሳቸው የሰው ስርዓቶች ሊኖሩ ይችላሉ ። ነገር ግን በጊዜያዊነት ነዋሪ ሰለሆንን ይህን እናደርጋለን ። እንግዳ ሁልጊዜም በአዕምሮ የሚያስበው መዳረሻ አለው። ለጊዜው ባለበት ቦታ በተለያዩ መልካም ነገሮች ደስ ሊሰኝ ይችላል ፤ ነገር ግን አሁንም መዳረሻውን አይረሳም ። ትኩረቱን ከመዳረሻው ላይ አይነቀልም ።

በዚህ ዘመን ብዙ ክርስቲያኖች በሰማይ ከተዘጋጀላቸው ድግስ ይልቅ የጊዜው የምድር ቅምሻ ላይ ትኩረታቸው ተወሰደ ሲባል ስለሞት ያለ መረዳት አንዱ ሊሆን ይችላል ። ሞት ወደ ህይወት መሻገሪያ ድልድይ እንደሆነ በብዙ መንገድ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል ። የእምነት አባቶቻችን ተቆጥሮ የተሰጣቸውን የዕድሜ ቁጥር በደንብ መንዝረው ለጌታ ክብር እና ፍቃድ የሚጠቀሙ በመሆናቸው ወደ ጌታ መሰብሰብን አብዝተው የሚመኙ ነበሩ።

**“በእነዚህም በሁለቱ እጨነቃለሁ፤ ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ፥ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና፤”**

**— ፊልጵስዩስ 1፥23**

ጌታ እራሱ እርሱን የሚከተል ሰው መኖሪያው ምድር ሳይሆን ሰማይ መሆኑን እንዲህ ሲል ተናግሯል ።

**“የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ፥ እኔም ባለሁበት አገልጋዬ ደግሞ በዚያ ይሆናል፤ የሚያገለግለኝም ቢኖር አብ ያከብረዋል።”**

**— ዮሐንስ 12፥26**

መጽሐፍ ቅዱስ ስለጌታ ተከታዮች ሲናገር እራሳቸውን ብቻ እያመቻቹ የሚኖሩ ሳይሆኑ ለክርስቶስ አካል ጊዜያቸውን ፣ ጉልበታቸውንና ዘመናቸውን የሰጡ ስለነበሩ ፤ ከዚህ ዓለም የሚጠብቁት ሽልማት አልነበራቸውም ፡ ይልቁንም ከጠራቸው እና ከሾማቸው ንጉስ ኢየሱስ እንጂ ።

**“የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ።”**

**— 1ኛ ጴጥሮስ 5፥4**

ሌላኛው ከዚህ ሀሳብ ጋር አብሮ ተያይዞ መነሳት ያለበት ለእግዚአብሔር መንግስት እና ፅድቅ ያለን ቦታ ነው። ሰዎች ስለሆንን መሠረታዊ የሚባሉ ፍላጎቶቻችን በአንድም በሌላም በሚታየው ዓለም ላይ ጥገኝነታችንን ይጨምራል። ምግብ ፣ ልብስ መጠለያ ለድርድር የማይቀርቡ የመኖር ህላዌያችንን የሚመረኩዙ ናቸው ብል በትልቁ የምሳሳት አይመስለኝም። ምክንያቱም በየቀኑ ሩጫችን እና ተጋድሎዓችን ይብዛም ይነስ እነዚህን ነገሮች ዋስትና መስጠት ስለሆነ ነው። መፅሐፍ ቅዱስ እነዚህ ሁሉ አያስፈልጉም ብሎ አይነግረንም። እንደውም እግዚአብሔር በረከቱንና ልግስናውን በእነዚህ ፍላጎቶቻችን ላይ እንደሚያሳይ ይነግረናል። የእስራኤል ልጆች ከሰማይ መና ጠል መጥገብ አንዱ ማሳያ ነው። ነገር ግን ነጋችንን በእነዚህ እንድንመሰርት እና የእምነት መልዕቆቻችን እንዲሆኑ እግዚአብሔር ፈቃዱ አይደለም። እግዚአብሔር ብቻውን የህይወታችን አቅርቦት ነው። እግዚአብሔር ህዝቡን ከሚፈትነበት ነገር አንዱ ምን ያህል የሚከተለው

እና የሚያመልከው ህዝብ በነገው ህይወቱ ላይ በእርሱ እንደሚታመን ማወቅ ይፈልጋል ። ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነን ከግብፅ ወደ ከነዓን ጉዞ ላይ የነበረውን የቃል ኪዳን ህዝብ እስራኤልን የፈተነበት (Litmus of faith ) ነው።

**“እግዚአብሔር ያዘዘው ነገር ይህ ነው፦ እያንዳንዱ የሚበላውን ያህል ይልቀም፤ በድንኳኑ ባሉት ነፍሶች ቍጥር ለአንድ ሰው አንድ ጎሞር ውሰዱ አላቸው።”**

**— ዘጸአት 16፥16**

**“ሙሴም፦ ማንም ከእርሱ አንዳች ለነገ አያስቀር አላቸው።”**

**— ዘጸአት 16፥19**

እስራኤላውያን ግን እግዚአብሔር ከእነርሱ የሚሻውን አይነት እምነት አልያዙም ነበር። ነገ የሚሆነው አይታወቅም በሚል ፍራቻ ለነገ የሚሆናቸውን መብል ማከማቸት እና ማጠራቀም ተያያዙት። ይህም የእግዚአብሔርን ባሪያ ሙሴን አሰቆጥቷል ፣ ግልባጩ ደግሞ እግዚአብሔርም ተቆጥቷል ፤ አዝኗል ማለት ነው። የሰው አፉ ታሟል ማለት ሰውዬው ታሟል ማለት ነው። ሙሴ የእግዚአብሔር አፍ ( መልዕክተኛ ) ነው።

**“ነገር ግን ሙሴን አልሰሙትም፤ አንዳንድ ሰዎችም ከእርሱ ለነገ አስቀሩ፥ እርሱም ተላ ሸተተም፤ ሙሴም ተቈጣቸው።”**

**— ዘጸአት 16፥20**

የሚደንቀው ነገር የሰበሰቡት ለነገ ሊሆንላቸው አለመቻሉ ነው። እግዚአብሔር የሌለበት የሀብት ክምችት ስለነበር ዕጣ ፈንታው ያለጥቅም ሆነ።

**“ሰውም ሁሉ ዕለት ዕለት የሚበላውን ያህል በጥዋት ለቀመ፤ ፀሐይም በተኰሰ ጊዜ ቀለጠ።”**

**— ዘጸአት 16፥21**

**ለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በመልዕክቱ ይህን ያሰፈረው።**

**“ብዙ ያከማቸ አላተረፈም፥ ጥቂትም ያከማቸ አላጎደለም።”**

**— 2ኛ ቆሮ 8፥15**

እግዚአብሔር በነገር ሁሉ መታመናችን በእርሱ ላይ እንዲሆን ይፈልጋል። አምላክ እና ጌታ ስለሆነ በሀይሉ ችሎት ላይ የሚደገፍን ህዝብ ይፈልጋል። እግዚአብሔር በመለኮታዊ ብቃቱ እና ሀይሉ በሚተማመን እና በሚደገፍ ህዝብ ደስ ይሰኛል። መፅሐፍ ቅዱስ ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት እንደማይቻል ይናገራል። እስራኤላውያን በምድረበዳ የመቅረታቸው ዋነኛ ምክንያት አለማመናቸው እንደሆነ እና እግዚአብሔርም በብዙዎች ደስ እንዳልተሰኘ ጳውሎስ ብዙ ሺህ ዘመናትን አቋርጦ አዲስ ኪዳን ላይ ይነግረናል።

**“እግዚአብሔር ግን ከእነርሱ በሚበዙት ደስ አላለውም፥ በምድረ በዳ ወድቀዋልና።”**

**— 1ኛ ቆሮንቶስ 10፥5**

ወደ እኛም የትኩረት አቅጣጫ ስንመጣ ከዚህ የተለየ ሆኖ አናገኘውም። ከፈረሱ ይልቅ ጋሪው ከቀደመ አስቸጋሪ ነው። ክርስትና ላይ ፈረሱ የእግዚአብሔር መንግስት እና ፅድቅ ነው። የእግዚአብሔርም ሀሳብ እና ፍላጎት ይህ ነው። ይህን አምነን እንቀበለው ዘንድ የተገባ የሰማይ አጀንዳ ነው። ፈረሱ እስከቀደመ ድረስ ጋሪው መከተሉ አይቀርም። ውሻን አንገቱ ላይ ሰንሰለት ተደርጎ ሲጎተት የውሻው ጭራ አብሮ እየተከተለ ይመጣል። ነገር ግን ሰንሰለቱን አንገቱ ላይ ሳይሆን ጭራው ላይ አድርገን ብንጎትት ውሻውን ወዴት እየወሰድነው እንደሆነ ግራ ያጋባል። በክርስትና ህይወት ውስጥም የሚከተሉን ነገሮች ላይ ስንጠላጠል ዋናውን ወደ መጣል እንደርሳለን።

**“ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።”**

— **ማቴዎስ 6፥33**

ስለዚህ አንድ ቀን ሂያጅ መሆናችንን መረዳት ትክክለኛ አስተሳሰብ ነው።

## 2. እንደ እንግዳ ለመኖር የምንዋጋው ጦርነት

**“ወዳጆች ሆይ፥ ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት ትርቁ ዘንድ እንግዶችና መጻተኞች እንደ መሆናችሁ እለምናችኋለሁ፤”**
**— 1ኛ ጴጥሮስ 2፥11**

በአንድ ወቅት የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪ እያለው እንደ እናት ያሳደገችኝ አክስቴ ቤት ውስጥ በዚያን ጊዜ ትሰራ ከነበረች የቤት ውስጥ ተቀጣሪ ጋር ወፍጮ ቤት አብሬ እንድሄድ ታደርገኝ ነበር። ያው የሚፈጨውን እህል አብረን ይዘን እንድንሄድ አስባ ማለት ነው። እናም የሆነ ጊዜ ደንበኞችን ጋር መብራት ጠፍቶ ስለነበር አቅራቢያ ወዳለ አንድ ሙስሊም ወፍጮ ቤት ሄድን። ወፍጮ ቤት ውስጥ የተፃፈ አንድ ጥቅስ ላለፉት ብዙ አመታት ከአዕምሮዬ አልጠፉም። “ ጀግና ሰው ማለት ሌላውን ታግሎ የሚጥል ሳይሆን በንዴት ጊዜ እራሱን የሚቆጣጠር ነው” የሚል ነበር። በእርግጥም እራስን ማሸነፍ ትልቅ ጀግንነትን ይጠይቃል ። ክርስትናም ሲጨመቅ በብርጭቆ ውስጥ የሚቀረው እራስን አሸንፎ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በእኛ ሁኔታ እንዲገለጥ መፍቀድ ነው። በአንድ ቤት ውስጥ ሁለት አባወራዎች ፣ በአንድ መንግስት ሁለት ንጉስ እንደማይኖር ሁሉ በአንድ መቅደስም ሁለት ጌታ ሊኖር አይችልም ። ስለዚህ አሮጌው አዳም መሰቀል አለበት። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን በሚገባ በመልዕክቱ ይነግረናል ;

**“ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።”**
**— ገላትያ 2፥20**

**“የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ።”**
**— ገላትያ 5፥24**

በአንዱ አዳም አለመታዘዝ ወደ ዓለም የገባው የሀጢያት ተፈጥሮ በትውልዶች ቅብብል ውስጥ ዕዳንና ኩነኔን አስከትሏል ። ጠላት ዲያቢሎስም ለዘመናት የሀጢያት ባርነትን በሰዎች ህይወት ውስጥ ቀንበር አሸክሞ ከእግዚአብሔር ሲያርቃቸው ቆይቷል። ሁሉ ስጋ ለባሽ ይሄ ነው የሚባል በእግዚአብሔር ፊት የሚያቀርበው ነገር አልነበረውም ፤ ይልቁንም ነብዩ ኢሳያስ እንደተናገረው ፅድቃችን የመርገም ጨርቅ ነበር።

**“ሁላችን እንደ ርኩስ ሰው ሆነናል፥ ጽድቃችንም ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው፤ ሁላችንም እንደ ቅጠል ረግፈናል፥ በደላችንም እንደ ነፋስ ወስዶናል።”**
**— ኢሳይያስ 64፥6**

ነገር ግን የምህረት አምላክ እግዚአብሔር ራርቶልን በአንድ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ዳግም ወለደን ፤ እርሱ ሀጢያታችንን ወስዶ በአብ ፊት የመቅረቢያ ድፍረት የሚሆነንን የእርሱን ፅድቅ አለበሰን። ሀሌሉያ !!! ጌታ እንዴት መልካም ነው። ሰማይ ትልቅ ርህራሄን አሳየን ;

**ቲቶ 3**
**4 ነገር ግን የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ፥**
**5 እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፥ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም፤**
**6-7 ያን መንፈስም፥ በጸጋው ጸድቀን በዘላለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን፥ በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትርፎ አፈሰሰው።**

ስለዚህ መስቀል ላይ በተደረገው ቤዛነት ለዘመናት ሲከሰን የነበረው የዕዳ ፅፈት ተሰረዘልን። በእኛ ላይ የበላይ የነበረው የሀጢያት ሀይል ስልጣኑ ተገፈፈ። አዲስን ጌታ በእኛነታችን ላይ ሾምን፤ ይህም ጌታ አልፋ እና ኦሜጋ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ምንም እንኳን አዳማዊ የሀጢያት ተፈጥሮ የነበረውን ሀይል እና የባርነት ቀንበር ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ጠርቆ ድል ቢነሳውም

**"ከኃጢአት ጋር እየተጋደላችሁ ገና ደምን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተቃወማችሁም፤ "**

**— ዕብራውያን 12፥4**

ክርስትና ውስጥ ድል አድራጊነት ያለው አንድን ውጊያ በማሸነፍ ሳይሆን ሙሉ ጦርነትን በድል በመወጣት ነው። ውጊያ የአንድ ወቅት እና ቦታ ነው ፤ ጦርነት ግን የህይወት ዘመን ውጊያዎች ድምር ነው። ዛሬ በስጋዬ ላይ ያገኘውት ድል አንድ እርምጃ ሊሆን ይችላል ፣ ነገር ግን በየዕለቱ የሚደረገው ውጊያን በጌታ ፀጋ ማሸነፍ ወሳኝ ነው። የጦርነት ሜዳው ደግሞ አዕምሮ ወይም ሀሳብ ነው። ጌታ በመስቀል ላይ ሰይጣንን አሸንፎታል ፤ አሁን ትልቁ የሰይጣን አቅም በስጋችን በኩል የሚያደርገው ሽንገላ ነው። የእርኩሰትንና ዓለማዊ ምኞት ሀሳብን ይዘራል ። ይህ ደግሞ ነፍስን የሚዋጋ እንደሆነ ሐዋርያው ጴጥሮስ በመልዕክቱ ይገልጻል ። እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ በሚሆን ፅድቅና ቅድስና የተፈጠረውን አዲሱን ሰው የሚዋጋ ስጋዊ ምኞት ነው። ስለዚህ የጦርነቱ ማዕከል ሀሳብ ከሆነ ፤ ሀሳባችንን በተቆጣጠርነው መጠን ነው የስጋ ምኞትን ማሸነፍ የምንችለው ማለት ነው።

የስጋ ምኞት ብዙ አይነትና መልክ ያለው ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በገላትያ መልዕቱ በደንብ ዘርዝሯል ።

**ገላትያ 5**
**19 የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፥ ርኵሰት፥ መዳራት፥**
**20 ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቁጣ፥ አድመኛነት፥ መለያየት፥ መናፍቅነት፥**
**21 ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።**

ሀሳባችን ላይ ብልጫ ከወሰድን ባህሪያችንን እንደ እግዚአብሔር ቃል ማነፅ እንችላለን ማለት ነው። ምንም ነገር ድርጊት ከመሆኑ በፊት በመጀመሪያ ሀሳብ ነበር። ይህን ትንሽ መጽሐፍ ከመፃፌ በፊት ለአንድ አመት ያህል ሀሳብ ነበር። "

Thought is the father of action" የሚባለው ለዚህ ነው። በጣም ላቅልለው እና የማታ ህልሞቻችን እንኳን ብዙውን ጊዜ የቀን ሀሳባችን ውጤት ናቸው። ይህ ሳይንሳዊ ማስረጃ የማያስፈልገው ይህን መጽሐፍ ባነበብንበት ቀን ባለው ሌሊት ማየት የምንችለው ነገር ነው።

ስለዚህ ክርስቲያን በዚህ ምድር ኑሮው እንግዳ እንደመሆኑ መጠን ከባህሪ ፣ ሀብት ፣ የተቃራኒ ፆታ ምኞት ጋር በተያያዘ ዕለት ዕለት ጦርነት ውስጥ ይገባል። በእርግጥም እግዚአብሔርን በእውነተኛ ማንነት ለመከተል የሚወድ ሁሉ በእነዚህ ፈተናዎች የተከበበ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ የተፈተኑ እግዚአብሔር በሀጢያት በጨቀየ ዓለም የፅድቅ ዛፍ አድርጎ የተጠቀማቸው ሰዎች አሉ። ኖህ እራሱ ከተከለው ወይን ጠጥቶ ሰከረ ፣ እንደ ልቤ የተባለው ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ተኝቶ በሀጢያት ወደቀ ፣ ኤልያስ ከኤልዛቤል ዛቻ የተነሳ እምነቱ ዋዥቅ ያቃል ፣ ሕዝቅያስ የእግዚአብሔርን ሀሳብ የሚያደርግ ንጉስ የነበረ ቢሆንም በመጨረሻዎቹ አመታት በኩራት ታበየ። እና አሸናፊ እነዚህን ብርቱ ሀያላን መጥቀሱ አሁን ላለንበት ድካም ሰበብ ለመስጠት ሳይሆን የስጋ ምኞት በእርግጥም አደገኛ መሆኑን እንደማሳያ ለማቅረብ ነው። እነርሱስ አካሄዳቸውን አስተካክለው ለእኛ ምሳሌ ሆነውልናል።

ብዙ ተስፋ ግን አለን። የተትረፈረፈ የእግዚአብሔር ፀጋ ፣ መንፈስ ቅዱስ ተሰጥቶናል። እኔ ስፅፈው ቀላል ይመስላል ፤ መሬት ላይ ሲወርድ ግን ከባድ እንደሆነ ይገባኛል ። ግን የልብ መሰጠትን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። እራስን ለክርስቶስ አሳልፎ መስጠት።

**ዕብራውያን 4**

**15 ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም።**

**16 እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ።**

**ገላትያ 5**

**16 ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ።**

...

**25 በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ።**

ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መረዳት የምንችለው ሁለት ሀሳብ አለ። የመጀመሪያው በኃጢአት ላይ ድል ለመቀዳጀት እንደ ክርስቲያን በእራሴ አልችልም ማለትን መልመድ አለብን። ምናልባት በዘህ ቅፅበት አዕምሮአችን ውስጥ የጳውሎስ መልዕክት ትዝ ብሎን ግራ ተጋብተን ሊሆን ይችላል ።

**“ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።”**
**— ፊልጵስዩስ 4፥13**

ግን ይህ ጥቅስ ጳውሎስ ስለራሱ ብቃት የተናገረበት እንዳልሆነ አማርኛ ማንበብ የሚችል ሁሉ በግልፅ የሚረዳው ነው። “ በክርስቶስ” ብሎ ነው የነበረበት ሁኔታን እንደሚያሸንፍ የተናገረው። ይህ ብቻ አይደለም ከቁጥር 11-13 ጳውሎስ አስቀድሞ ስለጌታ ሲል የተቀበለውን መከራ አስቀድሞ ፅፏል። ይህ አጥጋቢ ካልሆነ ደግሞ የሚቀጥለውን ክፍል ማየት ትክክለኛ አረዳድን ለመያዝ ያግዛል ;

**“ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ፤ ለእኔም የተሰጠኝ ጸጋው ከንቱ አልነበረም ከሁላቸው ይልቅ ግን ደከምሁ፥ ዳሩ ግን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም።”**
**— 1ኛ ቆሮንቶስ 15፥10**

ስለዚህ ጳውሎስ በክርስትና ውስጥ መከራ እና ፈተና የማይቀር እና አብሮ የተጠቀለለ የስጦታ መጠቅለያ እንደሆነ ተናግሮ መውጫው ግን የእግዚአብሔር ፀጋ እንደሆነ በሚገባ ተናግሯል ።

ስለዚህ በምህረቱ ባለጠጋ ወደሆነው አምላክ ዞሩን ፊት ምህረትን መጠየቅ እና ፀጋን በትህትና ልብ መቀበል የእኛ ድርሻ ነው።

ሁለተኛው ከጳውሎስ የገላትያ ምዕራፍ 5 መልዕክት መረዳት የምንችለው ሀጢያትን በተለይም የስጋን ምኞት የምናሸንፈው በመንፈስ መመላለስ ነው ( walking in the spirit). በመንፈስ መመላለስ እራስን ለመንፈስ ቅዱስ በፈቃደኝነት አስገዝቶ ዕለት ዕለት በእርሱ ቁጥጥር ስር መሆን ነው። ይህም መንፈስ ቅዱስ የአብን ፈቃድ በእኛ ውስጥ የመፈፀምን አቅም ይሰጠናል ። እኛነታችን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ከተገዛ አዳማዊው ማንነት እየሞተ ይሄዳል ።

ስለዚህ እንደ እንግዳ ለመኖር መያዝ የሚገባን ሌላው ነገር የምናዋጋው ጦርነት እንዳለ ነው : ይህም ከእራሳችን የስጋ ምኞት ጋር ነው።

## 3. እንደ እንግዳ ለመኖር ማዳበር ያለብን የህይወት ዘይቤ

**“ስለሚመለከቱት ስለ መልካም *ሥራችሁ፥* ክፉ እንደምታደርጉ በዚያ እናንተን በሚያሙበት ነገር፥ በሚጎበኝበት ቀን እግዚአብሔርን ያከብሩት ዘንድ በአሕዛብ መካከል ኑሮአችሁ መልካም ይሁን።”**

**—1ኛ ጴጥሮስ 2፥12**

“መልካም ስራ” ተብሎ በዚህ መልዕክት የተገለፀው ባህሪን ፣ ስርዓትን ፣ የኑሮ ሁኔታን ወይም ዘይቤን የሚያመለክት ነው።አጠቃላይ የህይወታችንን መዓዛ እና ጣዕም የሚያሳይ ነው። በአህዛብ መካከል የሚለው አግባባዊ ፍቺ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት እና ትንሳኤ የማያምኑ ዙሪያችን ያሉ ሰዎችን የሚያመለክት ነው። ምንም እንኳን ያልዳኑ ሰዎች በክርስቶስ ኢየሱስ የመቤዠት ስራ የማያምኑ እና መፅሐፍ ቅዱስን የማይቀበሉ ቢሆኑም የእኛን ገሀድ ህይወት አይተው የሆነ መልካም ነገር ሊያገኙብን ይገባል ። ይህም በሰማይ ያለውን አምላክ እንዲያከብሩ ምክንያት ይሆናል ።

**“መልካሙን *ሥራችሁን* አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።”**

**— ማቴዎስ 5፥16**

እንደ ክርስቲያን ጥሪያችን በራሱ የእግዚአብሔርን ክብር ማዕከል ያደረገ እንደሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ በመልዕቶቹ አፅንኦት ተሰጥቷል ።

**_“እንግዲህ የምትበሉ ወይም የምትጠጡ ብትሆኑ ወይም ማናቸውን ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት።”_**

**— 1ኛ ቆሮንቶስ 10፥31**

**_“መድኃኒታችንም ከዓመፅ ሁሉ እንዲቤዠን፥ መልካሙንም ለማድረግ የሚቀናውን ገንዘቡም የሚሆነውን ሕዝብ ለራሱ እንዲያነጻ፥ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቶአል።”_**

**— ቲቶ 2፥14**

ይህ ደግሞ ለብዙዎች የንስሐ ህይወት እና መዳንን የሚያመጣ እንደሆነ በተጠቀሱት ጥቅሶች ውስጥ ማግኘት ይቻላል ።

**_“እኔ ደግሞ ብዙዎቹ ይድኑ ዘንድ ለጥቅማቸው እንጂ የራሴን ጥቅም ሳልፈልግ በሁሉ ነገር ሰውን ሁሉ ደስ እንደማሰኝ፥ ለአይሁድም ለግሪክም ሰዎች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንም ማሰናከያ አትሁኑ።”_**

**— 1ኛ ቆሮንቶስ 10፥32-33**

ሐዋርያው ጴጥሮስም የጌታ የጉብኝት ቀን ( day of visitation ) ብሎ በጠራው የፍርድ ቀን ለእግዚአብሔር ምስጋና የሚሆን መዳን ለብዙዎች እንደሚያመጣ ተነግሯል ። ያቺ በተራራ ላይ ከፍ ብላ የምትታየው ከተማ ልትሰወር እንዳልተቻላት እኛም ብርሀን በሆነው ጌታ ብርሀን ስለተደረግን ፈለግንም አልፈለግን ያላመኑት ትኩረት እኛ ላይ ነው ያለው።

መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በስራ ትጋትን ስለማሳየት ምሳሌ ከሚሆኑን መካከል ገብረ ጉንዳን ናት። የተደራጀ እና የአመራር ሰንሰለት ( hierarchy ) ሳይኖራቸው በጣም ታታሪ እና ትጉ ፍጥረታት ናቸው። ሁሉን ነገር የሚያስተባብር አለቃ እና አዛዥ ሳይኖራቸው ለመኖር መሠረት የሚሆናቸውን ምግብ በበጋ ይሰበስባሉ ። እንደ ንብ የስልጣን ተዋረድ ሳይኖራቸው እና የበጋ ወቅት ሲደርስ ምግብ እንዲሰበስቡ

ምሪትን እና ኃላፊነትን የሚሰጣቸው መሪ ሳይኖር እነሱ ግን ወቅቱንም ኃላፊነታቸውንም ጠንቅቀው ያውቃሉ ።

**“ገብረ ጉንዳን ኃይል የሌላቸው ሕዝቦች ናቸው፥ ነገር ግን በበጋ መኖዋቸውን ይሰበስባሉ።”**

**— ምሳሌ 30፥25**

**ምሳሌ 6**

**6 አንተ ታካች፥ ወደ ገብረ ጉንዳን ሂድ፥ መንገድዋንም ተመልክተህ ጠቢብ ሁን።**

**7 አለቃና አዛዥ ገዢም ሳይኖራት፤**

**8 መብልዋን በበጋ ታሰናዳለች፥ መኖዋንም በመከር ትሰበስባለች።**

ከገብረ ጉንዳን ትልቅ ትጋትንና ሠራተኝነትን መውሰድ እንችላለን ። ታካችነት እና ስንፍና እግዚአብሔር ደስ የማይሰኝባቸው ነገሮች እንደሆኑ መፅሐፍ ቅዱስ በብዙ ማስረጃ ይነግረናል ። ገብረ ጉንዳን ከዚህ ታካችነት እና ስንፍና የራቁ ህዝቦች ናቸው። ከገብረ ጉንዳን ስራውን በፈቃደኝነት በወቅቱ መጀመር ፣ የተጀመረን ስራ መፈፀም እና መጨረስ እንዲሁም ከባድ ስራን ለማምለጥ ከመጣር ይልቅ እስከመጨረሻው መትጋትን እንማራለን ።

ትጋት እና ጠንካራ ሠራተኝነት በማያምኑት ዘንድ መታወቂያችን ሊሆኑ ይገባል ። በጥንቷ ቤተክርስቲያን ክርስቲያኖች በትጋታቸው እና ጠንካራ ሠራተኝነት በሚኖሩበት ማህበረሰብ ዘንድ ይታወቁ ነበር ። የተመረጡት በቃል እና ፀሎት ያገለግላሉ ፤ ሌሎች ደግሞ ሰርተው ካገኙት ላይ አምጥተው በህብረቱ መካከል ያኖራሉ ፣ የተቀሩት ማዕድን ያዘጋጃሉ።

**“በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤”**

**— ሐዋርያት 2፥46**

ይህ በጠንካራ ስራ እና ትጋት የታጀበ ህብረት በመካከላቸው ችግረኛ እስካይኖር ድረስ ሁሉም በቂ ህይወት እንዲኖር አድርጎት ነበር።

**“በመካከላቸው አንድ ስንኳ ችግረኛ አልነበረምና፤ መሬት ወይም ቤት ያላቸው ሁሉ እየሸጡ የተሸጠውን ዋጋ ያመጡ ነበርና፥”**

**— ሐዋርያት 4፥34**

አንድ ጎንደር ዩኒቨርስቲ የማውቀው በመንፈስ እና በእግዚአብሔር ቃል የበረታ መንድም አንድ ጊዜ በመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ የሰጠው ምሳሌ ለዚህ ፅሁፍ ብጠቀመው ብዬ አሰብኩ። ክርስቲያን ማለት ልክ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ መካከል ላይ መብራት በበራበት አስፓልት ላይ እንደሚራመድ ሰው ነው። አንድ ጊዜ የበራው አስፓልት ላይ ወጥቷል ፤ ዙሪያው በከበበው ጨለማ የሞላበት ጫካ ውስጥ ያለ የትኛውም ሰው አካሄዱንና ሁኔታውን ይመለከተዋል። ይህ ወንድሜ የሰጠው ምሳሌ በእርግጥም የአንድ ክርስቲያንን የምድር ህይወት የሚያሳይ ነው። በምድር እንግዶች እንደመሆናችን በመልካም ግብራችን የጨለመውን ዓለም ማብራት ፣ የመረረውን የሰው ልጅ ህይወት ማጣፈጥ ከጌታ የተቀበልነው አደራ ነው።

## 4. በመጠን መኖር

**“እንግዲያስ እንንቃ በመጠንም እንኑር እንጂ እንደ ሌሎች አናንቀላፋ።”**
**— ፲ኛ ተሰሎንቄ 5፥6**

በምንኖርበት ምድር ነገር ሁሉ በልክ ሲሆን ያምራል የሚለው አስተሳሰብ ብዙዎች የሚገዙት እና የሚቀበሉት ነው። ሰዎች ደስታ እና ሰላም የሚሰማቸው የተረጋጋ እና መቅበዝበዝ የሌለበት ህይወት ሲኖሩ ነው። መረጋጋት ደግሞ ያለው ለነገሮች ልክን እና መጠንን በማበጀት ውስጥ ነው። በመጠን መኖር ነገ ላይ ካለ ተስፋ አንፃር ተለክቶ ዛሬ ላይ ለመኖር የሚመረጥ የኑሮ ዘይቤ ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ በማዕበራዊ ህይወታችን የምናውቃቸው እንዲሁም አንዳንዶቹን የምንተገብራቸው ልምምዶች አሉ። ከጤና አንፃር ሳይንስ ካስገኘው የምርምር ውጤት ውስጥ የተመጣጠነ ምግብ ይጠቀሳል ። ምግብ ሁሉ ምግብ ስለሆነ ብቻ መመገብ ፍላጎትን ያረካ ይሆን ይሆናል እንጂ ነገ ላይ ተስፋ ለምናደርገው የተሟላ ጤና እቅፋት ነው። አንድ መኪና የሚነዳ ግለሰብ እንኳን መጠጥ ቤት ገብቶ ከመጠጥ ቤት ሲወጣ የሚነዳበትን መንገድ እያሰበ በልክ እና በመጠን ይጠጣል ። ከመጠን በላይ መጠጣቱ በትራፊክ ፖሊስ ስለሚያስቀጣው ብቻ ሳይሆን ጠጥቶ ማሽከርከር ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ ስለሚረዳ ነው። ጥሩ ክርስትያናዊ ምሳሌ ባይሆንም የምንወስደው ትምህርት ስላለ ነው። በብዙ ሰዎች መሀል የሚያወራ ሰው አንደበቱን ገትቶ ቃላቶቹን መጥኖ ይናገራል ። ምክንያቱም የአፍ ወለምታ አይታሽም እንደሚባለው ነገ ላይ ብዙ መዘዝ እና ተጠያቂነት የሚያመጡ ንግግሮችን አፍ እንዳመጣ መናገር ዛሬ ላይ ጥፋቱ ላይታይ ይችል ይሆናል ፤ ነገር ግን ነገ ላይ ጥፋትን አርግዞ መከሰቱ ሳይታለም የተፈታ ነው።

እነዚህ ሁሉ ምሳሌዎች መሠረታዊ የክርስትና የኑሮ አይነት የሆነውን በመጠን መኖር ለማንሳት ነው። በተለይ ደግሞ በእንግድነት ዘመናችን የተመጠነ አኗኗር መፅሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ መርህ ነው። የዚህ አኗኗር አስፈላጊነት ከጊዜው የምድር ኑሮ እና ቆይታ አንፃር ሳይሆን ከዘለዓለም መዳረሻችን አንፃር የሚታይ ነው። አሁን ያለን የምድር ቆይታማ ገንዘብን ብቻ እንድናሳድድ ፣ ማጋበስና መሰብሰብን ብቻ የህይወታችን ዓላማ አድርገን ጊዜያችንን ፣ ጉልበታችንን እና ትኩረታችንን ምድር ላይ ብቻ እንድንሰፋ የሚጋብዝ ነው። መስራት ፣ ገንዘብ ማግኘት ፣ ብልፅግና መልካም ነው ፡ እግዚአብሔርም በነዚህ ነገሮች እኛን መባረክ ደስታውና የመልካምነቱ አንድ ማሳያ ናቸው።

ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ትልቁን ስዕል እስኪሸፍኑብን ድረስ ያለመጠን አንድ አጥር ውስጥ አጥረው ሊያስቀምጡን አይገባም ። ብዙ የምናደርጋቸውን መንፈሳዊ ተግባራት እንዳናደርግ እስከመከልከል ሊደርሱ አይገባም ።አንዱ ማድረግ የሚገባን መንፈሳዊ ተግባር የነቃ ልብና መንፈስን መያዝ ነው። መንቃታችን እንደ ሌባ አመጣጥ የተመሠለውን የጌታ ዳግም ምፅዓት ከመጠባበቅ አንፃር ነው። ቀኑንና ሰዓቱን አለማወቃችን ደግሞ ምን ያህል የነቃ ክርስትና እንደሚያስፈልገን ማሳያ ነው።

አንድ ሌሊት ላይ ወደ ውጪ ሀገር በረራ ያለበት ሰው ቀን ላይ እንደማንኛውም ሰው ተመሳሳይ ተግባራትን ሊያደረግ ቢችልም ሁሉን ግን በመጠን ያደርጋል ። በረራ ላይ ሊረብሸው የሚችለውን ምግብ አይበላም ፣ ቀኑን ሙሉ ከወዳጆቹ ጋር በጨዋታ አያሳልፍም። ይልቁንም ማግኘት ያለበትን ሰው በጊዜ አግኝቶ ፣ መስራት ያለበትን ስራ በጊዜ ፈፅሞ ከበረራ ጋር ተስማሚ የሆነ ምግብ በልቶ በጊዜ ወደ ቤቱ ይገባና ለጉዞ የሚሆነውን ልብስ ፣ ሻንጣ ፣ ስንቅ ያዘጋጃል ከዛም ከበረራ ሰዓት አስቀድሞ አየር ማረፊያ መድረስ ስላለበት አላርም (alarm) ይሞላና የተወሰነ ሰዓት ይተኛል ። ሌላ ሰው ቢሆን ይህን ላያደርግ ይችላል ፤ ማድረግም አይጠበቅበትም። ምክንያቱም ተጓዡ እና በረራ ያለበት ብቻ ነው ይሄ የሚመለከተው። የእኛም የክርስቲያኖች የምድር ቆይታ ከዚህ የተለየ አይደለም ። የተሞላ አላርም ያስፈልገናል። ይሄ ሀሳብ የሚጎረብጠው ሰው ቀጣዮቹን የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አይቶ መቀበል ይጠበቅበታል ።

**“ከእንቅልፍ የምትነሡበት ሰዓት አሁን እንደ ደረሰ ዘመኑን እወቁ፤ ካመንንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን ዛሬ ወደ እኛ ቀርቦአልና።”**

**— ሮሜ 13፥11**

**2ኛ ጴጥሮስ 3**

**8 እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ፥ በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት፥ ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን እንደ ሆነ ይህን አንድ ነገር አትርሱ።**

**9 ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል።**

ምናልባት ማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 25 ላይ ያለውን የአስሩን ቆነጃጅት የእግዚአብሔር መንግስት ምሳሌ አንብበናል። ሰነፎቹ ሙሽራው ሲመጣ ግርግር ውስጥ የገቡት ቀን ያልሞሉትን ዘይት ሙሽራው በመጣ ጊዜ ለመሙላት በመጣደፋቸው ነው። ቀን ላይ በብዙ ነገር እራሳቸውን ወጥረው ልክ ያልተበጀለት ዉሎ ስለነበራቸው የሙሽራውን ድንገተኛ መምጣት ዘንግተውታል። ዛሬም ሀብት ፣ ዝና በሚሉ ስሜት ቆስቋሽ ነገሮች ትውልድን በምታሰክር ዓለም ውስጥ እኛ ግን በልክ መኖርን ምርጫችን አድርገን ለጌታ ቀን የነቃን እንሁን።

ግብራችን ልክ እንደ አምስቱ ልባም ቆነጃጅት ዘይታችንን በቀን እንሙላ። ዘይቶቻችን ሐዋርያው ጳውሎስ እና ጴጥሮስ በፃፉት መልኩ ተቀምጧል ።

**“እኛ ግን ከቀን ስለ ሆንን፥ የእምነትንና የፍቅርን ጥሩር የመዳንንም ተስፋ እንደ ራስ ቁር እየለበስን በመጠን እንኑር፤”**

**— 1ኛ ተሰሎንቄ 5፥8**

**“ስለዚህ የልቡናችሁን ወገብ ታጥቃችሁና በመጠን ኖራችሁ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ የምታገኙትን ጸጋ ፈጽማችሁ ተስፋ አድርጉ።”**

**— 1ኛ ጴጥሮስ 1፥13**

ሌላው በመጠን መኖራችን ለፀሎት ፣ ለእግዚአብሔር ቃል ፣ ከቅዱሳን ጋር ላለ ህብረት ጊዜ እንዲኖረን ያደርጋል ። ትምህርት ብቻ ፣ ስራ ብቻ ተደርጎ እየተመራ ያለ ህይወት ለእነዚህ መንፈሳዊ ተግባራት እምብዛም ቦታ እንዳንሰጥ እና ቸልተኛ እንድንሆን ያደርጋል ።

**“ትጸልዩም ዘንድ በመጠን ኑሩ፤ ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናልና ከሁሉ በፊት እርስ በርሳችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ።”**

**— 1ኛ ጴጥሮስ 4፥8**

**“በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤”**

**— 1ኛ ጴጥሮስ 5፥8**

ሌላው በመጠን መኖር በእግዚአብሔር ላይ የመታመናችን መገለጫ ነው። በእግዚአብሔር ላይ መታመን ነገ ሲታሰብ ስጋት እና ፍርሀት ሳይሆን ተስፋ እና የፀና እምነት መያዝ ነው። እግዚአብሔር ርስት ያደረገውን ህዝብ አይጥልም ደግሞም አይተወውም ።

**"ራሳችሁን ከፍቅረ ንዋይ ጠብቁ፤ ባላችሁ ነገር ረክታችሁ ኑሩ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር፣ "ከቶ አልተውህም፤ በፍጹም አልጥልህም" ብሎአል።"**

**— ዕብራውያን 13፥5 (አዲሱ መ.ት)**

ኤልያስ በዘመኑ የእግዚአብሔርን አጀንዳ በብዙ ነገስታት ዘመን ፈፅሞ ያለፈ ታላቅ እና ብርቱ ነብይ ነው። በህይወቱ ስለተገለጠው የእግዚአብሔር ኃይል ብዙ ማለት እንችላለን ። መፅሐፍ ቅዱስ ስለ ኤልያስ ከሚነግረን ነገር አንዱ በእግዚአብሔር ላይ ያለው መታመን ነው። በቀርሜሎስ ተራራ ከባዓል ነቢያት ጋር የተወራረደው ውርርድ ፣ ሰማይን መዝጋት እና መክፈት ፣ የመበለቲቱ ማድጋና ማሰሮ በተዓምራት መሙላት እና ወደሞት እየሄደ የነበረውን ልጇን ማዳን ወዘተ... በእስራኤል ምድር ዝናብ ባልዘነበ እና ድርቅ በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር ኤልያስን በተለየ የህይወት ካርታ አኑሮታል።

**1ኛ ነገሥት 17 (አዲሱ መ.ት)**

**2 ከዚያም እንዲህ የሚል የእግዚአብሔር ቃል ለኤልያስ መጣለት፤**

**3 "ከዚህ ተነሥተህ ወደ ምሥራቅ ሂድ፤ ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ባለው በኮራት ወንዝ ተሸሸግ።**

**4 ውሃ ከወንዙ ትጠጣለህ፤ ቍራዎችም እዚያው እንዲመግቡህ አዝዣለሁ።"**

የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ባለ ሁኔታ ወደእርሱ መጣ። በሰው የማሰብ ጥግ ሊደረስበት በማይችል ጥበብ እግዚአብሔር ለህይወቱ ያለውን እቅድ ተናገረው። ኤልያስ ለዚህ ድምፅ በመታዘዝ ምላሽን ሲሰጥ እናያለን ።

**"ስለዚህ እግዚአብሔር ያዘዘውን ፈጸመ፤ ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ወዳለው ወደ ኮራት ወንዝ ሄዶ በዚያ ተቀመጠ።"**

**— 1ኛ ነገሥት 17፥5 (አዲሱ መ.ት)**

ወደ ኤልያስ የመጣው የእግዚአብሔር ቃል ከኤልያስ ሁለት የመታዘዝ ባህሪያትን ይፈልጋል ። የመጀመሪያው ወደተባለው ስፍራ መሄድ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ መቀመጥ ነው። መቀመጥ መታመንን ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ላይ የማድረግ ማሰያ ነው። ኤልያስ የመጣውን የእግዚአብሔር ቃል አልተጠራጠርም። አቅራቢያ ወዳሉ አህዛብ ዘንድ ሄዶ ምግብን ሲለምን አንመለከትም ። የእግዚአብሔር ነገር አያስተማምንም ፤ ምናልባት መልዕክተኛው ቁራ አንድ ቀን ሳይመጣ ቢቀርስ ብሎ አንዳች ሀሳብ ሲገባው አንመለከትም ። ተስፋን የሰጠ የታመነ እንደሆነ በእርግጥም ተረድቶ ነበር። ስለዚህም እግዚአብሔር ቃሉን ጠበቀ።

***"ቍራዎችም ጧትና ማታ እንጀራና ሥጋ ያመጡለት ነበር፤ ውሃም ከወንዙ ይጠጣ ነበር። "***

***— 1ኛ ነገሥት 17፥6 (አዲሱ መ.ት)***

የእኛም ህይወት ከዚህ የተለየ አይደለም ። ሁልጊዜ ቁራ እና መና ይመጣልናል ማለት ሳይሆን በዚህ ተገማች ባልሆነ እና ተለዋዋጭ በሆነ ዓለም ውስጥ መኖሪያችን ዘላለማዊው እግዚአብሔር ነው። በእርሱ የምትታመን ነፍስ ደግሞ መልካም መሰማሪያዋ ከላይ ከአርያም ነው።

## 5. እንደ እንግዳ ለመኖር ማስታወስ የሚገባን ቀን

**"በዚያም ቀን በቅዱሳኑ ሊከብር፥ ምስክርነታችንንም አምናችኋልና በሚያምኑት ሁሉ ዘንድ ሊገረም ሲመጣ፥ ከጌታ ፊት ከኃይሉም ክብር ርቀው በዘላለም ጥፋት ይቀጣሉ።"**

**2ኛ ተሰሎንቄ 1፥9-10**

ስለጌታ ዳግም ምፅዓት ሳስብ ከሚያስገርሙኝ ነገሮች አንዱ ጌታችን እና ንጉሳችን ኢየሱስ ሲመጣ አንድም በአማኞች እምነት ሊደነቅ እና ሊገረም መምጣቱ ነው። በእምነታቸው እስከመጨረሻው በሚፀኑ እና ዘላለምን አሻግረው በማየት የጊዜውን የዓለም መከራ በትዕግሥት ድል በሚነሱት እርሱ የክብር ንጉስ ኢየሱስ ይገረማል።

ሐዋርያው ጴጥሮስ በምዕራፍ 2 መልዕክቱ ላይ ከሚያነሳቸው ሀሳቦች ውስጥ የምድር እንግድነት የሚያበቃበት አንድ ቀን እንዳለ ነው። ጴጥሮስ መልዕክቱን የፃፈላቸው ቅዱሳን በሮም የጨካኙ ኔሮ አገዛዝ ወቅት በፅሁፍ ሊገለፅ የማይችል መከራ እና ስደት እስከ ሞት ድረስ እየተጋፈጡ ነበር። አንዳንዶች በህይወት እያሉ ቆዳቸው እንደ እንስሳ ቆዳ እየተገፈፈ ፣ ስታዲየም በሚያክል መሰብሰቢያ ውስጥ ከአንበሶች ጋር እንዲጋፈጡ ተላልፈው እየተሰጡ ፣ በእሳት እየተቃጠሉ እና ሌላም ብዙ ነገር እየሆኑ በነበሩበት ወቅት ነው የፃፈው። በዚህ ሁሉ የህይወት ፈተና ውስጥ የሚያልፉትን አማኞች ነው በእምነታቸው አሁንም ፀንተው እንዲቀጥሉ እና ጌታ በክብር በሚገለጥበት ወቅት እንደማያፍርባቸው አስረግጦ የሚነግራቸው ። አንድ ቀን አለ ብሎ በአፅንኦት ይነግራቸዋል ።

ይህም ጌታችንና መድሀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በህያዋንና ሙታን ላይ ሊፈርድ የሚመጣበት ቀን ነው። ከላይ ከተነሳው ሀሳብ መረዳት የሚገባን መልካም ስራችንን ያ ሁሉ ይድናል ማለት አይደለም ። ልባቸውን ለዚህ መዳን የሚያቀኑ እንደሚኖሩ ሁሉ በአመፃ መንገዳቸው እና በእንቢተኝነት የሚቀጥሉ ይኖራሉ ። ሐዋሪያው ጴጥሮስ ካነሳው ሀሳብ እግዚአብሔር በሁለት መንገድ ይከብራል በዚያ የፍርድ ቀን። አንደኛው በምድር የእንግድነት ቆይታችን ጊዜ በመልካም አኗኗራችን ወደ እውነት መንገድ በሚመጡት ነፍሳት ደስ ተሰኝቶ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ምንም እንኳን በመልካም ምሳሌያችን ድነትን የማይቀበሉ ሊኖሩ የሚችሉ ቢኖሩም በክርስቲያኖች የፅድቅ ባህሪ እና መልካም አኗኗር ይከብራል ።

## ሁለቱ መታረቅ የሚገባቸው ፅንፎች

ለቃሉ ትክክለኛ አገላለጽ አግኝቼለት እንደሆነ እርግጠኛ አይደለሁም ። "ፅንፍ" የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ አሉታዊ ብለን ከፈረጅናቸው ሀሳቦች ጋር ተያይዞ የሚነሳ ቃል ነው። በይበልጥ ደግሞ በፖለቲካው ዓለም ውስጥ ተደጋግሞ የሚነገር ንግርት ነው ማለት ይቻላል ። ቃሉ ሚዛናዊነትን ለሳተ በአንድ መረዳት ላይ ብቻ ተንጠልጥሎ የሚቀነቀንን ሀሳብ ለመግለፅ የተሰጠ ስያሜ ነው።

የመፅሐፉ ዋና ሀሳብ የእንግድነት ኑሮ በመሆኑ ከዚህ መፅሐፍ ቅዱሳዊ ሀሳብ ጋር በተያያዘ ቅዱሱ የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት ውስጥ ሁለት መታረቅ የሚገባቸው አረዳዶች ወይም አስተሳሰቦች እንዳሉ ማየት ይቻላል ፤ እንደ ግለሰብ እኔ ተመልክቻለሁ። "መታረቅ የሚገባቸው" ከተባለ በመካከላቸው ጥል አለ ማለት ነው። ሁለቱም ፅንፎች የሚመዘኑት ዘላለምን መሠረት በማድረግ መሆን አለበት ፤ ደግሞም ነው።

የመጀመሪያው ማንነትን የመርሳት ዝንባሌ ብለው ጥሩ ይሆናል ። ይህም የሰማይ ዜግነትን ዘንግቶ በምድራዊ ነገር ብቻ የመሰፋት ችግር ነው።

**"እኛ ግን አገራችን በሰማይ ነው፤ ከዚያ የሚመጣውንም አዳኝ፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በናፍቆት እንጠባበቃለን፤"**

**— ፊልጵስዩስ 3፥20 (አዲሱ መ.ት)**

የሰማይ መንግስት ዜጎች እንደመሆናችን መጠን መተዳደሪያችን የሰማይ ህገ-መንግስት ነው ፡ ይህም ህገመንግስት የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መፅሐፍ ቅዱስ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ሙሉ ትኩረት ዘላለም ነው። በአይን የሚታየው ፣ ጊዜያዊው እና የሚጠፋው ምድር ሳይሆን ልዑል ብቻውን በሰማይ ያዘጋጀው መኖሪያ ላይ ያተኮረ ነው።

**"ይሁን እንጂ፣ እንደ ተጻፈው፣ "ዐይን ያላየውን፣ ጆሮ ያልሰማውን፣ የሰውም ልብ ያላሰበውን፣ እግዚአብሔር ለሚወዱት አዘጋጅቶአል፤""**

**— 1ኛ ቆሮንቶስ 2፥9 (አዲሱ መ.ት)**

ሰው ትኩረቱ በሄደበት ሁለንተናው ይከተላል ( where attention goes energy flows ) እንደሚባለው ለከበረው እና የጊዜ ገደብ ለማይበጅለት አምላክ ከእነክብሩ ለሚገኝበት የዘላለም ህይወት ሁለንተናችንን ሰጥተን መዘጋጀት እና መስራት አለብን። ጊዜያችንን ፣ ጉልበታችንን ፣ ገንዘባችንን በላይ በሰማይ ላለው መዝገብ ማፍሰስ ( invest ) ማድረግ ይገባናል ። የዘላለም ርስታችን ጋር ለሚያደርሰን መስራት እና መትጋት እንደሚገባን ነብዩ ኢሳያስ በመሲሐዊው ትንቢቱ ( messianic expectation ) እና ጌታችንና መድህኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌላት ተናግረዋል።

**"ገንዘባችሁን እንጀራ ባልሆነ ነገር ላይ ለምን ታጠፋላችሁ? በማያጠግብስ ነገር ላይ ለምን ጉልበታችሁን ትጨርሳላችሁ? ስሙ፤ እኔን ስሙኝ፤ መልካም የሆነውንም ብሉ፤ ነፍሳችሁም በጥሩ ምግብ ትደሰታለች።"**

**— ኢሳይያስ 55፥2 (አዲሱ መ.ት)**

**"ለሚጠፋ እንጀራ አትሥሩ፤ ነገር ግን የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር ምግብ ሥሩ፤ ለዚህም እግዚአብሔር አብ ማረጋገጫ ማኅተሙን በእርሱ ላይ አትሞአልና።""**

**— ዮሐንስ 6፥27 (አዲሱ መ.ት)**

የክርስቲያን ኑሮ ዘላለምን መሠረት ያደረገ ካልሆነ እጅግ በጣም አታካች እና ብኩን መሆኑ አያጠራጥርም ። ምክንያቱም ተስፋ በሌለው ዓለም ውስጥ ብቻውን ተስፋ የሆነውን ጌታ ተስፋ እያደረገ ካልኖረ ምንም ያህል ቢሰራ እና ቢጥር ሰማይ ያልመዘገበው ሀብት ነውና ቅሪት አይኖረውም ።

**""ከእኔ ጋር ያልሆነ ሁሉ ይቃወመኛል፤ ከእኔም ጋር የማይሰበስብ ሁሉ ይበትናል።"**

**— ማቴዎስ 12፥30 (አዲሱ መ.ት)**

ኀተራችን የሰማይ መሆን አለበት። እዛ ላይ የተሰበሰበ ሰማይ መዝግቦታል እና የክብር ሽልማትን ያቀዳጃል። የምድሩ ኀተራ የጊዜው እና ጠፊ ነው።

*“ነገ የሚሆነውን እንኳ አታውቁም። ሕይወታችሁ ምንድን ናት? ለጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፋሎት ናችሁ።”*

— *ያዕቆብ* 4፥14 (አዲሱ መ.ት)

በእንግድነት ዘመናችን የተጠራነው በሰማይ ያለውን እንድንመለከት እና ለዛ እንድንሰራ ነው።

**ቆላስይስ 3 (አዲሱ መ.ት)**

**¹ እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፣ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ በተቀመጠበት በላይ ያሉ ነገሮችን እሹ፤**

**² አሳባችሁም በላይ ባለው ላይ እንጂ በምድራዊ ነገር ላይ አይሁን።**

ሁለተኛው ፅንፍ በተለይም ደግሞ በተሰሎንቄ ቅዱሳን ዘንድ የተስተዋለ እንደሆነ ከሐዋርያው ጳውሎስ የአንደኛ ተሰሎንቄ መልዕክት መረዳት እንችላለን ። በተወሰነ ቅንነት እና መልካም የሆነውን የጌታን ዳግም መምጣት ከመናፈቅ የመጣ አረዳድ ነው።

በእርግጥ በተሰሎንቄ አማኞች ውስጥ ብዙዎች ወደ ጌታ እየተሰበሰቡ ስለነበር በሚታየው ነገር ተስፋ ከመቁረጥም የተነሳ ሊሆን ይችላል ።

*“ወንድሞች ሆይ፤ አንቀላፍተው ስላሉ ሰዎች ሳታውቁ እንድትቀሩ አንፈልግም፤ ደግሞም ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ሰዎች እንድታዝኑ አንሻም።”*

— 1ኛ ተሰሎንቄ 4፥13 (አዲሱ መ.ት)

ሰዎቹ ስራ መስራትን ትተው የጌታን ዳግም ምፅዓት ብቻ በመጠበቅ በመሀላቸው የስራ ባህል ጠፍቶ ነበር። ይህም የወንድማማች መዋደድን እንዳያጠፋ ፍራቻ እንዳለው ጳውሎስ በመልዕክቱ አስፍሯል። ምክንያቱም በመሀላቸው ስራን መስራት በመጥፋቱ አንደኛው በሌላኛው ላይ ጥገኛ እንዲሆን እና ተመፅዋች

ስለሚሆን በጊዜ ሂደት ፍቅርን እያቀዘቀዘ ስለሚሄድ ነው። ማንኛውም ሰው በቀላሉ መረዳት እንደሚችለው ሰዎች በሌሎች ላይ ጥገኛ እየሆኑ በሄዱ ቁጥር መከባበር እና ሰዋዊው ክብር እየተነካ ይመጣል ፤ አንዱ ለሌላው በሚያደርገው ድጋፍ እየተሰላቸ ስለሚመጣ ነው። ስለዚህም ጳውሎስ በእንግድነት ዘመናቸው የጌታን መምጣት እየተጠባበቁ መስራት እንደሚገባቸው ይከፍላቸዋል ።

**1ኛ ተሰሎንቄ 4 (አዲሱ መ.ት)**

**11 ከዚህ በፊት እንዳዘዝናችሁ በገዛ እጃችሁ ሥሩ፤ በጸጥታ ኑሩ፤ በራሳችሁ ጉዳይ ላይ ብቻ አተኵሩ።**

**12 ይውም በዕለት ተለት ኑሮአችሁ በውጭ ባሉት ዘንድ እንዲያስከብራችሁና በማንም ሰው ላይ ሸክም እንዳትሆኑ ነው።**

ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ መልዕክቱ እጅግ መሠረታዊ የክርስትና አኗኗር ዘይቤዎችን አብሮ ያነሳል። ስራን መስራት ፣ በፀጥታ መኖር ፣ ዓላማ ላይ ማተኮርን። በፀጥታ መኖር የሚለው ሀሳብ ከግብዝነት የራቀ ፣ የታይታ ያልሆነ ፣ የመንፈስን አንድነት ከሚያውኩ ነገሮችን መቆጠብን የሚያመለክት ሀሳብ ነው። ጌታ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን አጥብቆ ከሚያሳስባቸው ሀሳቦች አንዱ የፈሪሳውያን እርሾ የነበረው ግብዝነት ወይም የታይታ ኑሮ ነበር።

**“ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ፤ ያለዚያ በሰማያት ባለው አባታችሁ ዘንድ ዋጋ የላችሁም።”**

**— ማቴዎስ 6፥1**

ፈሪሳውያን ሲፀልዩ ለመታየት ብዙ ልምምዶችን ይከተላሉ። ጌታ ደግሞ የእግዚአብሔር መንግስት በእንደዚህ አይነት መንገድ ስለማይሰራ ደቀመዛሙርቱን ከዚህ የአስተሳሰብ እርሾ እንዲላቀቁ ብዙ ያስተምራቸው ነበር። ይህም ሐዋርያው ጳውሎስ ካነሳው የፀጥታ ኑሮ ጋር እጅና ጓንት እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

በራሳቹ ጉዳይ ላይ አተኩሩ ( mind your own business ) የሚለው ሀሳብ ደግሞ በአገባባዊው ፍቺ አንድ ጊዜ የገባችሁበት የክርስቶስ ህይወት አለ ፤ ስለዚህም በዙሪያቹ ከሚታየው እና ከሚሰማው ነገር በላይ ዘላለምን እየተመለከታችሁ በራሳቹ የህይወት ዛቢያ (axis ) ላይ አተኩሩ ማለቱ ነው። አንድ የመፅሐፍ ቅዱስ አስተማሪ ይህን ሀሳብ ሲገልፀው ልክ በሰልፉ ላይ እንዳለ እና ለሆነ ተልዕኮ (mission)እየተዘጋጀ እንዳለ ወታደር ፡ ከሰልፉ ፍንክች እንደማይል እኛም ከጀመርነው የፅዮን ጉዞ ወይም የሰማይ ጉዞ ዘንበል ማለት እንደሌለብን የሚያመለክት ሀሳብ ነው። የበረሃ ተጓዥ የሆነው ግመል ጭነትን ጀርባው ላይ ተሸክሞ ወይም ሸክፎ ረጅም መንገድን ሲሄድ የፊቱን መንገድ ብቻ እያየ ፤ ወደኃላ እንደማይመለከት ፤ የብዙ ውሾች ጩኸት እንደማያስደነገጠው እና እንደማያስፈራው እኛም የተሸከምነውን የሰማይ አጀንዳ በማሰብ ከፊታችን ወደታየልን ክብር ብቻ መጓዝ ይጠበቅብናል።

ስለዚህ እንደ ክርስቲያን እና የምድር እንግዶች እንደመሆናችን በጠንካራ የስራ ባህል በማያምኑት ዘንድ መታወቅ እንደሚገባን ጳውሎስ በተሰሎንቄ መልዕክቱ አስፍሯል ። ራሱ የእግዚአብሔር ቃል አገልጋይ ሆኖ ሳለ ሌሎች ላይ ላለመክበድ እና በጠንካራ ስራ ምሳሌ ሆኖ ለመገኘት እርሱ እና የወንጌል ባልደረቦቹ እንደሚሰሩ ተናግሯል ።

**“በገዛ እጃችን እየሠራን እንደክማለን። ሲረግሙን እንመርቃለን፤ ሲያሳድዱን እንታገሣለን፤ ”**

**— 1ኛ ቆሮንቶስ 4፥12 (አዲሱ መ.ት)**

**“ወንድሞች ሆይ፤ ጥረታችንንና ድካማችንን ታስታውሳላችሁ፤ በማንም ላይ ሸክም እንዳንሆን ሌሊትና ቀን እየሠራን ወንጌል ሰበክንላችሁ።”**

**— 1ኛ ተሰሎንቄ 2፥9 (አዲሱ መ.ት)**

ስራ ዘርፈ ብዙ ነው። በአገልግሎት ፣ በትምህርት በመሳሰሉት በጠንካራ ሰራተኝነት መታወቅ ይገባናል ። ታላቁ መምህራችን እና ጌታችን እንኳን በቃል እና በስራ የበረታ ነብይ መሆኑ በምድር ቆይታው ወቅት ተመስክሮለታል ።

**"እርሱም፣ "የሆነው ነገር ምንድን ነው?" አላቸው። እነርሱም እንዲህ አሉት፤ "በእግዚአብሔርና በሰው ሁሉ ፊት በተግባርና በቃል ብርቱ ነቢይ ስለ ነበረው ስለ ናዝሬቱ ኢየሱስ ነው፤"**

**— ሉቃስ 24፥19 (አዲሱ መ.ት)**

# የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት በህይወታችን ...

ሰዉ ሁሉ በህይወቱ ብዙ መሻት አለው። የሰው ልጅ ሲፈጠር አንዱ በተፈጥሮ የተጎናፀፈው ነገር መሻት ወይም መፈለግ ነው። ክርስቲያን መሆን ከዚህ የሚያላቅቅ አይደለም ። እንደዛ ቢሆንማ እያንዳንዱ የህይወታችን ጉዞ በፈተና የተሞላ ባልሆነ ነበር። መቼስ ይህን የሚክድ አማኝ አይኖርም። አማኝ የሚለው በትልቁ ይሰመርበት። ገና ከጅምሩ በኤደን ገነት ለሰው ወድቀት ምክንያት የሆነው ፈተና የመጣው በመሻት ነው። የሰው ልጅ አትብላ ከተባለው ፍሬ የመብላት ፍላጎት በውስጡ ሲያይልበት በላ። ይህ የመሻት ወይም ፍላጎት በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ በተለያየ መልኩ ይታያል ። በትምህርት ፣ በስራ በመሳሰሉት የህይወት ጉዞዎች ይንፀባረቃል ። ህይወት ውስጥ ደግሞ ብዙ ፈተና የሚሆንብን ነገር የእኛን ፍላጎት እና መሻት ከእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ጋር አስታርቆ እና አስማምቶ መሄድ ነው። ሁላችን በተለያየ የህይወት አጋጣሚ በዚህ ነገር ተፈትነናል። እንደ ተማሪ በትምህርታችን የእኛ መሻት እና የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ ፤ ሰራተኞች በስራ ቦታ ፤ በመንፈሳዊ ህይወታችን የእግዚአብሔር ፈቃድ እና ሌሎች ብዙ መዳሠሥ የምንችላቸው የህይወት መስኮች በዚህ ሀሳብ በአንድም በሌላ የሚነኩ ናቸው።

**"በሰው ልብ ብዙ አሳብ አለ፤ የእግዚአብሔር ምክር ግን እርሱ ይጸናል።"**

**— ምሳሌ 19፥21**

የእግዚአብሔር ሉዐላዊነት አንዱ ባህርይ ፈጣሪ መሆኑ ነው። የሁሉ ነገር ጀማሪ እና ፈጣሪ እርሱ ነው። የአንድ ነገር ፈጣሪ ለመባል ከተፈጠረው ነገር በፊት የመኖር ህላዌ ማግኘትን ይጠይቃል። ብዙ በዓለማችን ያሉ ፈጠራዎችን እና የቴክኖሎጂ ግኝቶችን ከተመለከትን ፈጠራዎቹን ለመስራት አንድ የተፈጠረ ቅንጣት መጠቀም የግድ አስፈልጓቸዋል። ከባዶ ተነስተው ምንም ነገር አልሰሩም። ለምሳሌ አውሮፕላንን የሰሩት ሁለቱ ወንድማማቾች ዊልበር ራይት እና ኦሊቨር ራይት አውሮፕላኑን ሲጀምሩ ትናንሽ የብረት ቅንጣቶች እንዲሁም የአልሙኒየም ንጥረ ነገር ከብዙ ከተጠቀሙት ነገሮች ውስጥ ይጠቀሳሉ። ውበት የሞላባቸው ልብሶች የሆኑ እንስሳትን ቆዳ መጠቀም አስፈልጓቸዋል። ሰው ከተፈጠረ ነገር ተነስቶ ሌላ ነገረን የመስራት ጥበብ በፈጣሪው የተቸረው ፍጡር ነው። የሚገርመው ብዙ ባለምጡቅ አዕምሮ ዓለማችንን የቀየሩ ታሪክ ሰሪዎች አዕምሮአቸው በፈጣሪ ተባርኮላቸው ነው። ስለዚህ በእያንዳንዱ በሚታዩ የቴክኖሎጂ ግኝቶች ውስጥ የእግዚአብሔር የፈጣሪነት ባህርይ ጎልቶ ይታያል።

ይህ በፍጥረት ውስጥ የጀመረው የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ሰማይንና ምድርን በመፍጠር አሀዱ ብሎ ጀምሯል። ይህም የሁሉ ነገር ጀማሪ መሆኑ እና ታላቅነቱን ያሳያል።

**“ሰማይንና ምድርን የሠራ እግዚአብሔር ከጽዮን ይባርከህ።”**

**— መዝሙር 134፥3**

**“አቤቱ፥ በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ የአንተ ነውና ታላቅነትና ኃይል፥ ክብርም፥ ድልና ግርማ ለአንተ ነው፤ አቤቱ፥ መንግሥት የአንተ ነው፥ አንተም በሁሉ ላይ ከፍ ከፍ ያልህ ራስ ነህ።”**

**— 1 ዜና 29፥1**

አዲስ ኪዳን ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ሀሳብ ድፍን አድርጎ ከእርሱ በቀር አንዳች የሰማይ እና የምድር ኃይል በፍጥረት ውስጥ እጁ እንደሌለበት ተናግሯል።

## ቆላስይስ 1

**15_16 እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፤ የሚታዩትና የማይታዩትም፥ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፥ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው፤ ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል፤**

**17 እርሱም ከሁሉ በፊት ነው ሁሉም በእርሱ ተጋጥሞአል።**

የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮትነት የሚያሳይ እና ፈጣሪነቱን የሚገልጽ ሀሳብ ነው። ሰማይና ምድር ሲፈጠሩ እግዚአብሔር ይሁን ያለበት ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው ሲል የእድሜን ጉዳይ ሳይሆን የሚገልፀው በስልጣን የበላይ መሆኑን ነው። በፍጥረት ሁሉ ላይ ባለስልጣን ነው። ሰማይ እና ምድር የተጋጠሙት በእርሱ የስልጣን ቃል ( word of command ) ነው። የሰው ልጅ ፈጣሪም እርሱ ነው። ይህ ጉዳይ በዓለም ላይ ከልዩነቶች ሁሉ ምናልባት ትልቁ ልዩነት ነው። የእግዚአብሔር ሰው ቢሊ ግራሃም አንድ ጊዜ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ሲያስተምሩ አንድ ተማሪ እስኪ የእግዚአብሔርን መኖር በተጨባጭ አሳየኝ ( prove ) ተብለው እንደተጠየቁ ተናግረዋል። ለቢሊ ግራሃም ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጅ በሙሉ ከባድ ጥያቄ ነው። ጥያቄውን ከባድ የሚያደርገው ደግሞ ትልቁ እግዚአብሔር በእኛ ትናንሽ ምናምንቴዎች መገለፅ ስለማይችል ነው። ለዚህ ነው የዳዊት ልጅ ጠቢቡ ሰለሞን የእግዚአብሔርን ቤት ሰርቶ ከጨረሰ በኃላ የሰማይ እና የምድር ፈጣሪ እንዴት ሰው በሰራው ቤት ውስጥ ሊኖር ይችላል በሚል የእግዚአብሔርን ትልቅነት ያወደሰው።

**“በውኑ እግዚአብሔር ከሰው ጋር በምድር ላይ ይኖራልን? እነሆ፥ ሰማይ ከሰማያትም በላይ ያለ ሰማይ ይይዝህ ዘንድ አይችልም ይልቁንስ እኔ የሠራሁት ቤት እንዴት ያንስ ይሆን?”**

**— 2 ዜና 6፥18**

እናም ቢሊ ግራሃም ከሰለሞን አውድ ተነስቶ ጥያቄውን ሊመልሱ እንደሚችሉ ግልጽ ነው። እግዚአብሔርን ላቦራቶሪ ውስጥ አንድ test tube ውስጥ አስገብቼ

፤ ይኸው እግዚአብሔር ብዬ ላሳይክ አልችልም። እርሱ ከሰው አዕምሮ በላይ የሆነ የማይደረስበት አምላክ ነው። ነገር ግን የሚታዩት ስራዎቹ የእርሱን መኖር ይናገራሉ። ሰማይና ምድር ፣ እንስሳት እና እፅዋት ፣ ቀንና ሌሊቱ ሲፈራረቅ ሰውን በማህፀን ሰርቶ ሲወለድ የእግዚአብሔርን መኖር በዚህ አውቃለሁ። ንግግራቸውን ሲቀጥሉ ከሁሉ በላይ አንድ ነገር የእግዚአብሔር መኖር አስረግጦ ይነግረኛል ፤ የውስጥ ህሊናዬ ይህን ሁሉ ነገር ስመለከት አንድ ፈጣሪ መኖሩን ያስረግጥልኛል ብለው መለሱ። ሁላችንንም የሚያስማማ ምላሽ ይመስለኛል። እኛ በእርሱ የተፈጠርን ፍጡራን ፈጣሪ የሆነውን እርሱን ልንገልፀው አንችልም።

**“እኔን በማኅፀን የፈጠረ እርሱንስ የፈጠረው አይደለምን? በማኅፀንስ ውስጥ የሠራን አንድ አይደለንምን?”**

**— ኢዮብ 31፥15**

እግዚአብሔር የሰው ልጅ ከነበረበት የክብር ህይወት በሰራው ኃጢአት ከነበረበት ክብር ሲጎድል ያንን ክብር በክርስቶስ በኩል መልሶታል። ማለትም ዳግም የእግዚአብሔር ቤተሰብ ሆነናል። ከሞተው ህሊናችን ነፅተን የእግዚአብሔር በአንድ ልጁ በማመን የዘላለም ህይወት ወራሾች ሆነናል። ይህም የሀይሉ ታላቅነት ይመሰገን ዘንድ እንደበጎ ፈቃዱ ከዘላለም በፊት ፈጥሮን ለዚህ ክብር አበቃን።

**“ዓለም ሳይፈጠር፥ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን።”**

**— ኤፌሶን 1፥4**

**“እንደ ፈቃዱ ምክር ሁሉን የሚሠራ እንደ እርሱ አሳብ፥ አስቀድመን የተወሰንን በክርስቶስ ደግሞ ርስትን ተቀበልን።”**

**— ኤፌሶን 1፥11**

በቤተክርስቲያን ውስጥ አንዳንድ ጊዜ ለልዩነት መነሻ ምክንያት የሆነ ጉዳይ ነው መመረጥ ፤ መወሰን (predeterminism )። እርሱን ብዙ ያጠኑ ሰዎች

ቢያብራሩት መልካም ነው። የእኔ ትኩረት ግን እንደ እግዚአብሔር ፅድቅ እና ምሳሌ የተፈጠረው አዲሱ ሰው መልካም ባህርይ ተገኝቶበት እና ብቁ ሆኖ ሳይሆን እንዲው በፀጋው የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት አደረገው የሚል ነው። ፅድቅ አስቆጥረን ሳይሆን የኢየሱስ ፅድቅ ተቆጥሮልን ነው ፤ የሚታይ ማንነት ኖሮን ሳይሆን እርሱ ኢየሱስ ታይቶልን ነው። ስለዚህ አዲስ ፍጥረት የሆነውን ሰው በክርስቶስ በማቅረብ ውስጥ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ታይቷል።

**“እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፥ የሚኰንንስ ማን ነው?”**

**— ሮሜ 8፥33**

ሌላው የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት በግለሰብ ህይወት ውስጥ የመወሰን ስልጣን ነው። በተለይም ደግሞ መፅሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በአሮጌውም ሆነ በአዲሱ ኪዳን እግዚአብሔር የግለሰቦችን ህይወት እርሱ በወደደው መልኩ ፍፃሜ ሲያበጅ እንመለከታለን። የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ የፈርዖንን ቤት ንግስና እና ጮማ ጥሎ ወጥቶ ከርስቱ ህዝብ ጋር መከራን ቢቀበልም በእስራኤል ልጆች የደነደነ ልብ ምክንያት አለቱን ሁለት ጊዜ በመምታቱ ወተት እና ማር ወደምታፈልቀው ምድር ከነዓን አትገባም ተብሏል። ፃድቅ የነበረው ኢዮብ እግዚአብሔር የባሪያውን እምነት ሊፈትሽ በህይወቱ ልጆቹን ከማጣት ጀምሮ ያለው ሀብት ሁሉ በአንድ ጀምበር እንደ ጠዋት ጤዛ ሲረግፍ የኢዮብ ምላሽ እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔር ነሳ የሚል ነበር።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ በትልቁ የሚታየው የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት በጌታ ኢየሱስ ላይ ባደረገው የመስቀል ስራ ነው። ከጌቴሰማኔ የጀመረው የመከራ ፅዋ ጎልጎታ ላይ እስከደረሰው ጣረ ሞት ድረስ አባት ዓለምን ለማዳን ሲል ልጁን የተወበት ሉዓላዊ ምርጫ ነው።

**“በቀባኸው በቅዱሱ ብላቴናህ በኢየሱስ ላይ ሄሮድስና ጴንጤናዊው ጲላጦስ ከአሕዛብና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር፥ እጅህና አሳብህ እንዲሆን አስቀድመው የወሰኑትን ሁሉ ሊፈጽሙ፥ በዚች ከተማ በእውነት ተሰበሰቡ።”**

**— ሐዋርያት 4፥27-28**

ከጌታ ኢየሱስ በኃላ የቀጠለው ሰማዕትነት በሐዋሪያቱ ቀጥሎ ተንፀባርቋል። ጌታ ኢየሱስ ከትንሳኤው በኃላ ገና ለአገልግሎት እንኳን ያልተለየውን ጴጥሮስ እንዴት በወንጌል ምክንያት እንደሚሞት አስቀድሞ ነግሮታል።

**ዮሐንስ 21**

---

**18 እውነት እውነት እልሃለሁ፥ አንተ ጕልማሳ ሳለህ ወገብህን በገዛ ራስህ ታጥቀህ ወደምትወደው ትሄድ ነበር፤ ነገር ግን በሸመገልህ ጊዜ እጆችህን ትዘረጋለህ፥ ሌላውም ያስታጥቅሃል ወደማትወደውም ይወስድሃል አለው።**

**19 በምን ዓይነት ሞት እግዚአብሔርን ያከብር ዘንድ እንዳለው ሲያመለክት ይህን አለ። ይህንም ብሎ፡- ተከተለኝ አለው።**

በሮም አደባባይ ላይ ሊሰቅሉት ሲሉ እንደጌታዬ መሰቀል አይገባኝም ገልብጣቹ ስቀሉኝ ብሎ እንደሞተ የሚነገርለት ከአስራ ሁለቱ መካከል አንዱ የሆነው ሐዋርያው ጴጥሮስ በመጨረሻ መልዕክቱም ላይ ሞቱን አስመልክቶ ሊሞት ከሰማይ የተወሰነበት ጊዜ እንደመጣ ተናግሯል።

**“ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመለከተኝ ከዚህ ማደሪያዬ መለየቴ ፈጥኖ እንዲሆን አውቃለሁና።”**

**— 2ኛ ጴጥሮስ 1፥14**

እግዚአብሔር የሰውን የምድር ቆይታ ጊዜ የመወሰን ስልጣን ያለው ሉዓላዊ አምላክ ነው። የጌታ መንገድ ጠራጊ የነበረው መጥምቁ ዮሐንስ ጌታ አገልግሎቱን ከጀመረ በኃላ ሙሽራው ኢየሱስ እና ሚዜው ዮሐንስ እኩል አንድ ወንበር ላይ መቀመጥ ስለሌለባቸው እግዚአብሔር ዮሐንስ አንገቱ ተቆርጦ እንዲሞት ወሰነበት። ሚዜው ለሙሽራው ሁሉን ነገር ካሰናዳ በኃላ ተሰናበተ። ለምን ብዙዎችን ወደ ንስሐ የመለሰ ሰው በእንደዚህ አይነት ሞት እንዲሞት እግዚአብሔር ፈቀደ ተብሎ አይጠየቅም። እግዚአብሔር ፃድቅ ነው።

የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት በዚህ መልኩ በተለያየ አውድ ካየን አሁን ደግሞ በእያንዳንዳችን የግል ህይወት በተለይም እንግዶች ሆነን በምንኖርበት የምድር ቆይታችን የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ምን ይመስላል የሚለውን በተወሰነ ብንዳስስ መልካም ነው። አይደለም በእኔ ጀማሪ ፀሐፊ እና ገና የክርስትናን ጣዕም በደንብ ያላጣጣመ ወጣት ልጅ ይቅር እና በእግዚአብሔር ቤት ብዙ ዘመን የቆዩ እንኳን ከህይወታቸው ከባድ ተግዳሮቶች ጥቀሱ ቢባሉ አንዱ ሊሆን የሚችለው የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት ከራሳቸው መሻት እና ፍላጎት ጋር አጣጥሞ መሄድ ነው። መፅሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ሰው ሸክላ ሰሪ እጅ ላይ እንዳለ ጭቃ ተመስሏል። አንድ ሸክላ ሰሪ ከምድር አፈር ጭቃውን በወደደው ቅርፅ እና መጠን ይሰራዋል። የሸክላ ሰሪው ዋና ዓላማ የጭቃውን ምቾት መጠበቅ ሳይሆን ሸክላውን እርሱ የሚፈልገውን አገልግሎት እንዲሰጠው አድርጎ መስራት ነው። እርሱ የሚፈልገው አይነት ቅርፅ እስኪመጣለት ድረስ ወደዚህ እና ወደዚያ እያደረገ ይጠፈጥፈዋል። ይህን ሁሉ የሚያደርገው በሸክላው ላይ ባለቤት ስለሆነ እና ስልጣን ስላለው ነው። እግዚአብሔርም እንደዚሁ የህይወታችን ሸክላ ሰሪ ነው። እስራኤላውያን ከአምላካቸው ከእግዚአብሔር ህግ እና ትዕዛዝ እርቀው በልባቸው ሽንገላ እና ምኞት በዓሊምን እስከመከተል እና እስከማምለክ በደረሱበት ወቅት እግዚአብሔር በነብዩ ኤርሚያስ አማካኝነት እንደገና አምላክ እንደሚሆንላቸው እና እነርሱም ህዝብ እንደሚሆኑት ለመናገር ኤርምያስን ወደ አንድ ሸክላ ሰሪ ቤት ላከው። የእግዚአብሔርን ቃል ታዞ ወደ ሸክላ ሰሪው ቤት በሄደ ጊዜ ሸክላው በሸክላ ሰሪው እጅ ላይ ተሰበረ። እናም ሸክላ ሰሪው የተሰበረውን ጭቃ እንደገና መልሶ ሌላ ዕቃ አድርጎ ሰራው። የእግዚአብሔርም ዓላማ ለህዝቡ እንደዚሁ እንደሆነ እግዚአብሔር ለነብዩ አስገነዘበው። እስራኤላውያን ግን ለዚህ የተዘጋጁ አልነበሩም። እኛም አምላካችን እና መጠጊያችን እግዚአብሔር ነው። በእኛ ላይ ሙሉ ስልጣን ያለው እርሱ ነው።

***"የእስራኤል ቤት ሆይ፥ ይህ ሸክላ ሠሪ እንደሚሠራ በውኑ እኔ በእናንተ ዘንድ መሥራት አይቻለኝምን? እነሆ፥ ጭቃው በሸክላ ሠሪ እጅ እንዳለ፥ እንዲሁ እናንተ በእኔ እጅ አላችሁ።"***

**— ኤርምያስ 18፥6**

ታዲያ ጠብ እና ግጭት የሚመጣው ጭቃው ራሱ በሚፈልገው ቅርፅ እና መጠን መሰራትን ምርጫው አድርጎ ከሰሪው እጅ ለመላቀቅ ትግል ሲጀምር ነው። በዚህ ትግል ውስጥ መላላጥ እና መጀመሪያ ከነበረው ቅርፅ መፈረካከስ ይመጣል። ቀስ በቀስም ከሰሪው እጅ መወደቅ እና መሰባበር ይመጣል። ሸክላ ደግሞ በባህሪው ተሰባሪ ነው። ልክ እንደ ብረት መቆልመም እና መጣመም ሳይሆን መሰባበር ዕጣፈንታው ይሆናል። ምናልባት አስቸጋሪ እና አታካች ቢሆንም ሰሪው እጅ ላይ ቢቆይ ከመሰባበር ይድናል ፤ ይህ ትልቁ ዋስትና ነው። የስራው ወራት ካለፈ በኃላ ደግሞ ጊዜያዊ የነበረው ችግር እና ስቃይ የሚመስለው የመሰራት ወራት ክብርን ይዞለት ይመጣል። እኛም በህይወታችን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ፣ ዕቅድ እና አጀንዳ ጋር በአንድም በሌላም አጋጣሚ የጭቃውን አይነት ትግል እና ግጭት ውስጥ እንገባለን። ምክንያቱ ደግሞ እኛም ሰዋዊ በሆነው ማንነታችን ፈቃድ የሚባል የነፍስ ክፍል ስለተሰጠን ነው። ይህ ፈቃዳችን ልክ ኮርቻን እንደተጫነች አህያ ነው። ኮርቻው የአህያዋ ወገብ ላይ ተደርጎ በግራ እና ቀኝ የሆዷ ክፍል እህል ወይም ሌላ ነገር ይጫንባታል። በሁለቱም የኮርቻ ክፍል እኩል ክብደት ያለው ጭነት ካልተደረገ ብዙ ክብደት ያለው ጭነት በተጫነበት ኮርቻው ያጋድላል። የእኛም ፈቃድ አዕምሮአችን ውስጥ እንደገባው የእውቀት አይነት እና መጠን ወሳኔ ሰጪነቱ ያጋድላል። ለዛ ነው መፅሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ክፍሎች ላይ ስለእውቀት አስፈላጊነት የሚናገረው።

**“ነፍስ እውቀት የሌለባት ትሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ እግሩንም የሚያፈጥን ከመንገድ ይስታል።”**

**— ምሳሌ 19፥2**

**“ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል፤ አንተም እውቀትን ጠልተሃልና እኔ ካህን እንዳትሆነኝ እጠላሃለሁ፤ የአምላክህንም ሕግ ረስተሃልና እኔ ደግሞ ልጆችህን እረሳለሁ።”**

**— ሆሴዕ 4፥6**

አንድ ኮምፒውተር እየተጠቀመ ያለ ሰው የኮምፒውተሩ keyboard ላይ የሚፅፈው ማንኛውም ነገር የኮምፒውተሩ ስክሪን ( monitor ) ላይ ይታያል። ምክንያቱም ከውጪኛው የኮምፒውተር ክፍል ወደ ውስጠኛው የኮምፒውተር

ክፍል ያስገባው መረጃ ነው ውጤት ሆኖ መጨረሻ ላይ የሚገለጠው። ጌታ ኢየሱስ በትምህርቶቹ ውስጥ ከውጭ ወደውስጥ ስለምናገባው እውቀት የሚያስገኝ መረጃ አፅንኦት ሰጥቶ ተናግሯል።

**"እንግዲህ እንዴት እንድትሰሙ ተጠበቁ፤ ላለው ሁሉ ይሰጠዋልና፥ ከሌለውም ሁሉ፥ ያው ያለው የሚመስለው እንኳ ይወሰድበታል።"**

**— ሉቃስ 8፥18**

**"ከአፍ የሚወጣ ግን ከልብ ይወጣል፥ ሰውንም የሚያረክሰው ያ ነው።"**

**— ማቴዎስ 15፥18**

የገባ ነገር ሁሉ መውጣቱ ስለማይቀር መልካም ሆኖ የገባው መልካም ሆኖ ከልብ መዝገብ ይወጣል። ስለዚህም ወደልባችን የምናስገባው እውቀት የፈቃዳችንን ዛቢያ የመቆጣጠር አቅም አለው። እናም ከዚህ የተነሳ አንዳንዴ ከእግዚአብሔር ሉዓላዊ ፈቃድ ጋር ሙግት ውስጥ እንገባለን። ግን ደግሞ ምርጫ የሌለው የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ህይወታችንን እንዲገዛ መፍቀድ አለብን። ይህን የእግዚአብሔር በሸክላ ሰሪ ማንነት መመሰል መፅሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በተለያየ ቦታ ተገልጾ እናገኘዋለን።

## ሮሜ 9

---

**20 ነገር ግን፥ አንተ ሰው ሆይ፥ ለእግዚአብሔር የምትመልስ ማን ነህ? ሥራ ሠሪውን፦ ስለ ምን እንዲህ አድርገህ ሠራኸኝ ይለዋልን?**

**21 ወይም ሸክላ ሠሪ ከአንዱ ጭቃ ክፍል አንዱን ዕቃ ለክብር አንዱንም ለውርደት ሊሠራ በጭቃ ላይ ሥልጣን የለውምን?**

**"ከሠሪው ጋር ለሚታገል ወዮለት! በምድር ሸክላዎች መካከል ያለ ሸክላ ነው። ጭቃ ሠሪውን፦ ምን ትሠራለህ? ወይስ ሥራህ፦ እጅ የለውም ይላልን?"**

**— ኢሳይያስ 45፥9**

ይህ የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ባህርይ ጭቆና እና ባርነት ሳይሆን ከእርሱ የሁሉ ነገር ባለቤትነት የሚመነጭ በመሆኑ ሁሉን በእርሱ ላይ ጥለን እንድንደገፈው የሚያደርገን ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ለታመነለት ህዝብ መጠጊያ እና መሸሸጊያ ስለሆነ ነው። በምድር ላይ የሚሆኑ የትኞቹም ነገሮች ከእግዚአብሔር እውቅና ውጪ የሚሆኑ አይደሉም። የሚወጡ የህይወት እጣዎች ሁሉ እንዴት በየመደቡ መፈረጅ እንዳለበት አምላካችን ያውቃል።

**“ዕጣ በጕያ ይጣላል፤ መደብዋ ሁሉ ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።”**

**— ምሳሌ 16፥33**

ይህ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት በህይወታችን እንድንደላደል የሚያደርገን ከእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት የሚቀዳ በመሆኑ ነው። በየትኛውም የህይወት አጋጣሚ ሀሳቡን ከመፈፀም የሚከለክለው አንዳች የሰማይ እና የምድር ሀይል የለም። እግዚአብሔር በሀይል ብርቱ ፣ በቅድስናው አስፈሪ ማንም ሊተካከለው አይችልም። ስለሁሉ ነገር ሁሉን የሚያውቅ አምላክ ነው ፤ የራስ ፀጉራችንን በቁጥር የሚያውቅ ንጉሥ ነው። ስለዚህ አንድ ስንኳ የፀጉር ዘለላ ያለ እርሱ ፈቃድ አትወድም ፤ ስለዚህም በህይወቴ በሚሆነው ነገር ሁሉ እርሱ ብቻውን እንዲገዛኝ እፈቅድለታለሁ።

**“ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደ ሆንህ፥ አሳብህም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ።”**

**— ኢዮብ 42፥2**

## ማቴዎስ 10

**29 ሁለት ድንቢጦች በአምስት ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ከእነርሱም አንዲቱ ያለ አባታችሁ ፈቃድ በምድር ላይ አትወድቅም።**

**30 የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ ተቈጥሮአል።**

**31 እንግዲህ አትፍሩ ከብዙ ድንቢጦች እናንተ ትበልጣላችሁ።**

የልጅ ጥያቄ የዘመናት የለቅሶ ምክንያት የሆነበት የሐና ቤት አንድ ቀን መለኮታዊ ጉብኝትን አስተናገደና ለህዝብ መፍትሔ የሆነ ነብይ ተወለደ። ሐናም የለቅሶ ዘመኖቿን በሚቀጥለው ፅሁፍ ማሳረጊያ አበጅታ እኛን ጨምሮ ለብዙ ትውልድ የህይወት አቋም ሆነ።

**1ኛ ሳሙኤል 2**

---

**6 እግዚአብሔር ይገድላል ያድናልም፤ ወደ ሲኦል ያወርዳል፥ ያወጣል።**

**7 እግዚአብሔር ድሀ ያደርጋል፥ ባለጠጋም ያደርጋል፤ ያዋርዳል፥ ደግሞም ከፍ ከፍ ያደርጋል።**

**8 ከሕዝቡ መኳንንት ጋር ያስቀምጣቸው ዘንድ፥ የክብርንም ዙፋን ያወርሳቸው ዘንድ፥ ችግረኛውን ከመሬት ያስነሣል፥ ምስኪኑንም ከጉድፍ ያስነሣል፤ የምድር መሠረቶች የእግዚአብሔር ናቸውና፥ በእነርሱ ላይም ዓለምን አደረገ።**

ነገር ሁሉ ለበጎ ነው ፤ የመፅናኛ ቃል ሳይሆን የመልካም ነገሮች ሁሉ ምንጭ የሆነው እግዚአብሔር በህይወታችን የነገሰ ብቸኛ ንጉሥ ስለሆነ ልጆቹን እንዴት መምራት እንዳለበት ያውቃል።

**“እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።”**

**— ሮሜ 8፥28**

# እጅ ከምን

የሆነ ወቅት ላይ የአንድን ታላቅ የወንጌል አገልጋይ መፅሐፍ እያነበብኩ ከዛ ቀደም ህይወቴን አስቤው በማላውቀው ሁኔታ እንዳስበው አደረገኝ። ጸሐፊው በእድሜው የመጨረሻ አመታት የፃፈው መፅሐፍ ነበር። አጠቃላይ የመፅሐፉ ጭብጥ እግዚአብሔር ምድር ላይ ፈቅዶ በሰጠን እድሜ እርሱ ለፈጠረን ዓላማ መኖር እንዳለብን የሚያወሳ ነው። ልቤን ከነኩት ነገሮች ውስጥ አንዱ ሰዎች በእድሜያቸው የመጨረሻ ዘመናት በተለይም ደግሞ የረዘመ የሽምግልና ዘመን ላይ ሲሆኑ እንዴት የምድር ቆይታቸው ከዛ በኃላ እንደሚያስጠላቸው እና ምናልባት ወደኃላ ተመልሰው በወጣትነታቸው ማስተካከል የሚገባቸው ነገር ብዙ እንደሆነ ግን ደግሞ በምንም ተዓምር ተመልሰው ይህን እድል እንደማያገኙ ሲያስቡ ምን ያህል እንደሚፀፀቱ ሲገባኝ አሁን በዚህ ጉብዝናዬ ከእግዚአብሔር በቸርነት የተቀበልኩት እድሜ ምን ያህል ውድ እንደሆነ እና በምድር ላይ ትልቁ የዋጋ ተመን የማይወጣለት እንደሆነ ማሰብ ጀመርኩ። በጊዜው አጥንቴ ውስጥ የሚነድድ ሀሳብ ስለነበር ለአንዳንድ ወዳጆቼ ሀሳቡን አካፍያለው። እግዚአብሔር ዘመን ሲያመጣ ደግሞ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ማካተትን መረጥሁ።

ምንም እንኳን በዚህ ምድር እንግዳ ብንሆን መዝገባችን በሰማይ ሲከፈት እጅ ከምን መባላችን አይቀርም። ይህን ሀሳብ እንዳነሳ መሠረት የሆነኝ የምርጡ መምህራችን እና ጌታችን የተናገረው አንድ የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው።

**“ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባኛል፤ ማንም ሊሠራ የማይችልባት ሌሊት ትመጣለች።”**

**— ዮሐንስ 9፥4**

ጌታ ኢየሱስ ይህን የተናገረው አጠገቡ ዕውር አይቶ ነው።

**“ሲያልፍም ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር የሆነውን ሰው አየ።”**

**— ዮሐንስ 9፥1**

ጌታ ሲያልፍ መስራት ያለበት ስራ እንዳለው ተረድቶ በምድር ላይ ተተምኖ በአባቱ የተሰጠው ጊዜ ሳያበቃ እንደሚሰራ ተናግሮ የዕውሩን አይን አበራ። ለምን መስራት እንዳለበት ደግሞ ሲናገር ወደ ምድር ሲመጣ ብርሀን ሆኖ እንደሆነ ተናግሯል ።

**“በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ።”**

**— ዮሐንስ 9፥5**

እኛም ተማሪዎቹ በምድር ላይ ያለን የቤት ስራ የመምህራችን አይነት ነው። እርሱ የዓለም ብርሀን እንደሆነ ሁሉ እኛንም ብርሀን እና ጨው አድርጎናል ።

**ማቴዎስ 5**

**13 እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፍጣል? ወደ ውጭ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ወደ ፊት ለምንም አይጠቅምም።**

**14 እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ። በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም።**

ብርሀን እና ጨው የተደረግነው ደግሞ ለስራ እንደሆነ እዛው ማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ላይ ሁለት ቁጥር በረድ ብሎ ይናገራል ።

***“መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።”***

**— ማቴዎስ 5፥16**

ጨው የተፈጠረበት ዓላማ የሚታየው ወጥ ውስጥ ሲገባ እንጂ በጓደኞቹ መካከል ሲመላለስ እና ሲፎክር አይደለም ። ጓደኞቹ እራሳቸው ጨው ስለሆኑ እርሱ

ያለው ተልዕኮ አላቸው ። ወይም ደግሞ አንድ መደርደሪያ ላይ ያለ ጨው እና መንገድ ላይ የተቀመጠ ድንጋይ ተመሣሣይ ናቸው ፤ ጨዉ ማጣፈጥ ያለበት ነገር ውስጥ እስካልገባ ድረስ ።

ክርስቲያን ጥሪው ብርሀን እና ጨው ሆኖ ዕውር እና መራራ በሆነው ዓለም ላይ እንዲገለጥ ነው። ቤተክርስቲያን ውስጥ ከቅዱሳን ጋር አብሮ ከመፀለይ ፣ ከመዘመር ያለፈ ተልዕኮ አለው።

ጌታ ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር መንግስት ሲናገር ካነሳቸው ሀሳቦች መካከል መክሊትን የሚመለከት ይገኝበታል። ምሳሌውንም በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 25 ላይ እናገኘዋለን። ወደሌላ አገር ተጓዥ የሆነ ሰው በወቅቱ ለነበሩት ባሮች እርሱ ያለውን ገንዘብ ሰጣቸው።

**“ወደ ሌላ አገር የሚሄድ ሰው ባሮቹን ጠርቶ ያለውን ገንዘብ እንደ ሰጣቸው እንዲሁ ይሆናልና፤”**

**— ማቴዎስ 25፥14**

ሶስት ሰዎች የተለያየ መክሊት እንደ አቅማቸው ተሰጣቸው። ከሄደበት አገር ሲመለስ ትርፍን ብቻ ጠብቆ ነው። ኪሳራን አይጠብቅም ፤ ይህም ብቻ ሳይሆን የሰጠው ገንዘብ ሳይቀንስ ሳይጨምር እንዲቀርብለትም አይፈልግም።

**“ለእያንዳንዱ እንደ ዓቅሙ፥ ለአንዱ አምስት መክሊት ለአንዱ ሁለት ለአንዱም አንድ ሰጠና ወደ ሌላ አገር ወዲያው ሄደ።”**

**— ማቴዎስ 25፥15**

ሶስቱ ሰዎች ከባድ አደራ እንደተጣለባቸው አያጠያይቅም። ምክንያቱም ጌታቸውን ደስ ለማሰኘት ማትረፍ ይጠበቅባቸዋል። የገቡበት ንግድ ( business ) አለማትረፍን እንደ ዕዳ የሚቆጥር ስለሆነ ሁለንተናቸውን ሰጥተው መስራት ይጠበቅባቸዋል። እርሱ ከሄደ በኃላ ሁሉም ወደስራ ገቡ። ሁለቱ የጌታቸውን አደራ እና የታማኝነት ሸክም እንዲሁም ኃላፊነት በሚገባ የተረዱ ናቸው። የገቡበት ንግድ ( business ) ራዕይ እና ተልዕኮ በደንብ የተረዱ በመሆናቸው

ማትረፍን ብቻ መሰረት አድርገው ነው ስራቸውን የሰሩት። ስለዚህም የመረዳታቸው እና ኃላፊነትን የማወቅ መጠናቸው ባስገኙት ውጤት ተንፀባርቋል። ሁለቱም እንደተሰጣቸው መጠን የተሰጣቸውን የሚመጥን ውጤት አመጡ። አምስት የተሰጠው አስር ፤ ሁለት የተሰጠው ደግሞ አምስት እንደተቀበለው አስር አድረጎ ማምጣት አይጠበቅበትም። ምክንያቱም የተሰጠው ሁለት ስለሆነ የሁለት መክሊት ጥያቄ ነው የሚቀርብለት ፤ ስለዚህም ሁለት አትርፎ በአጠቃላይ አራት ይዞ ቀረበ።

**ማቴዎስ 25**

---

**16 አምስት መክሊትም የተቀበለው ሄዶ ነገደበት ሌላም አምስት አተረፈ፤**

**17 እንዲሁም ሁለት የተቀበለው ሌላ ሁለት አተረፈ።**

ሶስተኛው ባሪያ ግን ከሁለቱ ባሮች ፍፁም የተለየ እሳቤ ነው ስለ ንግዱ የነበረው። ሁለቱ በተረዱት ተመሳሳይ አረዳድ ሳይሆን ከራስ በፈለቀ ቁንፅል አስተሳሰብ ነበር ንግዱን የጀመረው። ለራሱ የሰጠው ማሳመኛ ከሰበብ ያልዘለለ ስንፍና ነበር። ኃላፊነቱን ተረድቶ አደራውን ለመወጣት መትጋት ሲገባው ታካችነትን መረጠ። ለራሱ የሰጠው ምክንያት ኃላፊነትን ከእርሱ ለማሸሽ የተደረገ እጥፋት ነው ማለት ይችላል። ስለዚህም የተቀበለውን አንድ ታላንት ወይም መክሊት እንደወረደ መሬት ውስጥ ቀበረው።

**“አንድ የተቀበለው ግን ሄዶ ምድርን ቈፈረና የጌታውን ገንዘብ ቀበረ።”**

**— ማቴዎስ 25፥18**

ጌታቸው ያለውን ገንዘብ የሰጣቸው ትልቅ እምነት ጥሎባቸው ነው። ደግሞ በጣም እርግጠኛ ነው እንደማያሳፍሩት ምክንያቱም ካለው ላይ ቀንሶ እንደው ቢያከስሩኝስ ብሎ አይደለም የሰጣቸው ፤ ያለውን ሀብት ነው የሰጣቸው። ስለዚህ ከሄደበት አገር ትርፉን አስልቶ ፤ አትራፊውን ሊሸልም መጣ። ሁለቱን ባሮች በጠበቃቸው የታማኝነት ልክ ስላገኛቸው ያዘጋጀላቸውን የደስታ ድግስ ተካፋይ አደረጋቸው። ለሁለቱም ተመሣሣይ የምስጋና ክብር አቀረበ።

**"ጌታውም፡- መልካም፥ አንተ በጎ፥ ታማኝም ባሪያ፤ በጥቂቱ ታምነሃል፥ በብዙ እሾምሃለሁ፥ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው።"**

**— ማቴዎስ 25፥23**

ለሶስተኛው ባሪያ ግን የተለየ ዓለም ነው የጠበቀው። ሁለቱ ግቡ የሚል ግብዣ ሲዘጋጅላቸው ለእርሱ ግን ውጣ የሚል ፍርድ ተወሰነበት። በእርግጥም አደራን ሳይወጡ መቅረት ከባድ ነው። ታማኝነትን ማጉደል በአደራ ሰጪው ዘንድ መቅለልን ያመጣል። የነበረችው አንዷ መክሊት መወሰዷ ብቻ ሳይሆን ጨለማ ውስጥ መጣል እጣፈንታው ሆነ።

**"የማይጠቅመውንም ባሪያ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።"**

**— ማቴዎስ 25፥30**

ይሄ ጨለማ ውስጥ የተጣለው ባሪያ የማይጠቅም ተብሎ በጌታው ተፈረጀ። የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ጠቃሚዎች ናቸው ማለት ነው። ጠቃሚ ባሪያ ለተሰጠው አደራ የሚታመን እና የማያሳፍር ነው። ጌታ ኢየሱስ በእዚህ ምሳሌ ውስጥ የተናገረው ሀሳብ እጅግ መሠረታዊ ብቻ ሳይሆን ቀጣይ ለማነሳው ሀሳብ መንደርደሪያ የሚሆነኝ ነው።

**"ላለው ሁሉ ይሰጠዋልና ይበዛለትማል፤ ከሌለው ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል።"**

**— ማቴዎስ 25፥29**

በገረፍታ ሲታይ ላለው መጨመሩ አንድ ነገር ሆኖ ሳለ ፤ ከሌለው ላይ ግን የሚወስድበት ምን ኖሮት ነው ያስብላል። በመጀመሪያ መረዳት የሚያስፈልገው ያልተሰጠው ሰው አለመኖሩን ነው። በአውዱ ይህን የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል ከፈታነው ይህ የጌታ ኢየሱስ ንግግር የሶስቱን ባሮች አስታኮ የተደረገ መሆኑ ነው። ሶስቱም ባሮች አንዱ አምስት ፣ አንዱ ሁለት ፣ ሌላኛው ደግሞ አንድ ተሰጥቷቸው ነበር። ግን ጌታችን ያወራው መጀመሪያ በተሰጣቸው መክሊት ስላተረፉት ትርፍ

ነው። አምስት መክሊት የተሰጠው ሌላ አምስት በማትረፉ ባለው ላይ ተጨመረለት ፤ ክፉ እና ሃኬተኛ የተባለው ባሪያ ግን አንድ መክሊት ተሰጥቶት በተሰጠው ምንም ስላላተረፈ መጀመሪያ አትርፍበት ተብሎ የተሰጠው እንኳን ተወሰደበት።

በአንግድነት ዘመናችን ጌታ ለእያንዳንዳችን የሰጠን መክሊት አለ። ከላይ የተብራራው የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል ለዚህ ማስረጃ ነው። ጌታ ያንን ምሳሌ የሰጠው ለትምህርቱ ማጣፈጫነት ሳይሆን የእግዚአብሔርን መንግስት ሚስጥር ለደቀመዛሙርቱ እየገለጠላቸው ነበር። ጌታው እራሱ ጌታችን እና መድህኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ባሮቹ ደግሞ በጊዜው ደቀመዛሙርቱ አሁን ደግሞ እኛ ነን። ደስታው ደግሞ መንግስተ ሰማይ ነው። እኛም ዛሬ ስለመክሊታችን ማሰብ ይገባናል። እግዚአብሔር እጃችን ላይ ባኖረው ነገር ነው መስራት የወደደውን በህይወታችን የሚሰራው። በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር የተለያዩ ሰዎችን የትላልቅ የእግዚአብሔር እጅ መገለጫዎች ያደረጋቸው መጀመሪያ እነርሱ ዘንድ ያላቸውን ጠይቋቸው ነው።

እግዚአብሔር አምላክ ርስት አድርጎ የጠራውን የእስራኤል ህዝብ ከግብፅ አራት መቶ ሰላሳ አመት ባርነት ማስለቀቅ ሲፈልግ ሙሴን አገልጋዩ ማድረግ ወደደ። ሙሴ ግን በተደጋጋሚ ለዚህ ጥሪ የሚመጥን ሰው እንዳልሆነ እና ብቁ እንዳልሆነ ለእግዚአብሔር በማስረዳት ክርክር ውስጥ ገባ። በእርግጥ ሙሴ ትሁት ስለሆነም ሊሆን ይችላል። ዋናው ነጥብ ግን እግዚአብሔር ኮልታፋ እና አፈትብ በሆነው ሰው ሚሊዮኖችን ከባርነት ማውጣት መርጧል። ከሙሴ አቅም እና ችሎት በላይ የሆነ መለኮታዊ እጅ ነው ይህን የነፃ መውጣት እንቅስቃሴ የሚመራው። ይህን ለማድረግ እግዚአብሔር ሙሴን አንድ ነገር ጠየቀው። እጅህ ላይ ምን አለ የሚል ጥያቄ ነበር።

**“እግዚአብሔርም፦ ይህች በእጅህ ያለችው ምንድር ናት? አለው። እርሱም፦ በትር ናት አለ።”**

**— ዘጸአት 4፥2**

የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ መልስ ሊሆን የሚችለው የያዘው ነገር ነው። በዚህ ሰዓት ደግሞ እጁ ላይ የነበረው በትር ነበር። በምድያም አገር የአማቱን ዮቶር በግ የሚጠብቅባት ትንሽ በትር የእግዚአብሔር የማዳን ስራ ውስጥ ድንገተኛ በሚመስል ግን በእግዚአብሔር ዘንድ በታሰበ ዕቅድ ገባች።

በዚህች በትር እግዚአብሔር ፈርዖንን ምን አይነት አምላክ እንደሆነ ተዋወቀው ፤ የኤርትራ ባህር እንደ ግድግዳ ለሁለት ተከፈለ ፤ አለት ተሰንጥቆበት ምድረበዳ ላይ ያለ ህዝብ ውሃ ጠጣ ፤ ሙሴ በትሩን ከፍ አድርጎ አማሌቅ ላይ እስራኤላውያን ድል ይነሱ ነበር። ይህ ሁሉ በዚህች ትንሽ በትር ምልክትነት ሆነ። እዚህ ጋር የተሳሳተ አረዳድ እንዳይኖር ሁሉን ያደረገው የእግዚአብሔር የፀና ክንድ ነው። የሙሴ በትር ግን ምክንያት ተደረገች።

ሌላው የሙሴን አይነት ተመሣሣይ ጥያቄ የተጠየቀው የእስራኤል የምጥ ዘመን ነብይ የነበረው ኤርምያስ ነው። ከብንያም ካህናት አንዱ የሆነው የኬልቅያስ ልጅ ነብዩ ኤርሚያስ ምድርን ሳይተዋወቅ የእግዚአብሔር አጀንዳ ያረፈበት ሰው ነበር። ሳይወለድ ለነብይነት የተጠራ ነበር። ንጉስ ሴዴቅያስ በነገሰ በአስራ ሶስተኛው ዓመት ኤርሚያስ እና አስቀድሞ የታሰበው የእግዚአብሔር አጀንዳ ተገናኙ። ኤርሚያስም እንደ ሙሴ ለዚህ ጥሪ ብቁ እንዳልሆነ እና ብላቴና እንደሆነ ለእግዚአብሔር ተናገረ። እግዚአብሔር ግን የመረጠው እርሱ እንደሆነ እና በእርምጃው ሁሉ አብሮት እንደሆነ ከነገረው በኃላ ቃሉን አንደበቱ ላይ አኖረው። ቀጥሎም ምን ታያለህ የሚል መልኩን በተወሰነ የቀየረ ግን በሀሳብ ተመሣሣይ ጥያቄ እግዚአብሔር ለኤርምያስ አቀረበ።

**“ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል። ኤርምያስ ሆይ፥ ምን ታያለህ? እያለ ወደ እኔ መጣ። እኔም። የለውዝ በትር አያለሁ አልሁ።”**

**— ኤርምያስ 1፥11**

የኤርምያስ እይታ እግዚአብሔር በኤርምያስ ሊያደርገው ላለው ሀሳብ ምክንያት ሆነ። ምክንያቱም ተከታዩ የእግዚአብሔር ምላሽ ይህን ስለሚያስረዳ ነው።

**“እግዚአብሔርም፦ እፈጽመው ዘንድ በቃሌ እተጋለሁና መልካም አይተሃል አለኝ።”**

**— ኤርምያስ 1፥12**

እግዚአብሔር በኤርምያስ አማካኝነት ለእስራኤል እና ይሁዳ ቤት ብዙ ሊሆኑ የነበሩ ጉዳዮችን ተናግሯል።

ብዙ የስብከት ርዕስ ያልሆነ እና ስሙ የማይነሳ አንድ ልጅ አዲስ ኪዳን ውስጥ አለ። ለሺህ ዘመናት እየተነገረ ላለ የጌታ ኢየሱስ ተዓምር ምክንያት የሆነ ነው። ቀናትን ኢየሱስ እግር ስር ቁጭ ብሎ ሲማር ለነበረ እና ምግብ በአፉ ላልዞረ ህዝብ መመገብ ምክንያት የሆነው አምስት እንጀራ እና ሁለት አፍ መገኛ ነበር። ደቀመዛሙርቱን ምግብ ፍለጋ ከተማ ለከተማ መንከራተት ያተረፈ ነበር። በእርግጥ ከተማም ቢሄዱ ወንዶች ብቻ አምስ ሺህ ፤ አጠቃላይ መላው ህዝብ ደግሞ አስራ አምስት ሺህ ይደርሳል ተብሎ ለሚገመት ህዝብ ምን ያህል ገዝተው ይችላሉ የሚለው አስቸጋሪ ነው። ይሄ አሳ እና እንጀራ ባይኖርም ጌታ ሌላ የተዓምር ምክንያት ሊኖረው ይችላል። ግን ይሄ ታዳጊ ምክንያት ሆነ።

**“እነርሱም፦ ከአምስት እንጀራና ከሁለት ዓሣ በቀር በዚህ የለንም አሉት።”**

**— ማቴዎስ 14፥17**

በእነዚህ ሁሉ ሰዎች እግዚአብሔር ባላቸው ነገር ትልቅን ስራ ሰርቷል። ዛሬ ላይ ያለን ክርስቲያንኖችም ልዩ ልዩ የተሰጡን መክሊቶች አሉ። አንዳንዶቻችን ለቤተክርስቲያን ከተሰጡ የአገልግሎት ፀጋዎች አንፃር ይመለከተናል።

**“እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤”**

**— ኤፌሶን 4፥11**

ሌሎቻችን ደግሞ በተለያየ የህይወት መስመር ውስጥ ብርሀን እና ጨው የተረግንበት ማንነት አለ።

**ሮሜ 12**

---

**6 እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን፤ ትንቢት ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገር፤**

**7 አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ፤ የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ፤**

**8 የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ፤ የሚሰጥ በልግስና ይስጥ፤ የሚገዛ በትጋት ይግዛ፤ የሚምር በደስታ ይማር።**

በክርስቶስ አካል ውስጥ ብዙ ብልቶች አሉ። የብልቶቹ ሚና የተለያየ ነው። መቼስ አይን የጆሮን ሚና ሊተካ አይችልም ፤ እጅ የእግርን ሚና ሊተካ አይችልም። ሁሉ እንደተፈጠረበት ዓላማ ያገለግላል። አንዱ የሌላውን ሚና መተካት አለመቻሉ የአካል ብልቶች ሁሉ አስፈላጊ እና ጠቃሚ መሆናቸውን ያሳያል። በክርስቶስ አካል ውስጥም አንድ ብቻ አገልግሎት የለም። ጌታ እንደወደደ ለቤተክርስቲያን ጥቅም ለሁላችን የተለያየ ፀጋን ሰጥቶናል።

**1ኛ ቆሮንቶስ 12**

---

**4 የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው፤**

**5 አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው፤**

**6 አሠራርም ልዩ ልዩ ነው፥ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው።**

በእርግጥ ክርስትና የመጨመር ህይወት ነው። ዕለት ዕለት የሚበዛ ህይወት ለመኖር ተጠርተናል። ይህ ህይወት የክርስቶስ ህይወት ነው። ጌታችን በምድር ላይ የኖረውን አይነት እግዚአብሔር አብን ያስደሰተ ህይወት እንድንኖር ይጠበቅብናል።

**“ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ።”**

**— ዮሐንስ 10፥10**

የበዛ ህይወት በነገር ሁሉ ኢየሱስን በመምሰል የሚያድግ ህይወት ነው። ኢየሱስ በሰው መሀል ሲመላለስ የገለጠውን የእግዚአብሔርን ባህሪ እየገለጡ መኖር ያለበት ህይወት ነው። ለዚህም ነው ክርስትና ታድጎ የሚጨረስበት ሳይሆን ዕለት ዕለት የመጨመር ህይወት ነው የሚባለው። ሐዋርያው ጴጥሮስ ክርስትና የመጨመር ህይወት መሆኑን በሁለተኛ መልዕክቱ ላይ የገለፀው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በ2ኛው መልዕክቱ መሠረታዊ የክርስትና አኗኗርን ያነሳል። ክርስትና የመጨመር መለኮታዊ ትዕዛዝ ያለበት ህይወት እንደሆነ አስፍሯል ።

**2ኛ ጴጥሮስ 1**

**5 ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፥**

**6 በበጎነትም እውቀትን፥ በእውቀትም ራስን መግዛት፥ ራስንም በመግዛት መጽናትን፥ በመጽናትም እግዚአብሔርን መምሰል፥**

**7 እግዚአብሔርንም በመምሰል የወንድማማችን መዋደድ፥ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ።**

መለኮታዊ ሀይሉ የመለኮታዊ ባህሪ ተካፋይ እንድንሆን እና በዚህ መለኮታዊ ባህሪ ውስጥ እንድንሳተፍ አቅምን ሰጥቶናል። ይህ መለኮታዊ ባህሪ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ መታተም እና የመንፈስን ፍሬዎች ማፍራትን የሚያመለክት ነው። በእነዚህ መለኮትን በሚያከብሩ ባህሪያት ማደግ እና መጨመር እንዳለብን ቀጥሎ ይናገራል።

የክርስትና መሠረቱ በክርስቶስ ኢየሱስ የመስቀል ቤዛነት ያለ እምነት መሆኑ እሙን ነው። ማመን አንድ ነገር ነው ፤ ባህሪ ደግሞ ሌላ።

**በጎነት** : በእግዚአብሔር ላይ ያለን እምነት ከሀጢአት ይልቅ ወደ በጎነት ሊመራን ይገባል ። ይህም ግብረገባዊ ልዕቀትን ( moral excellence ) ያሳያል ።

**እውቀት** (knowledge ) : እግዚአብሔርን በማወቅ ማደግ ፤ በቃሉ በኩል ማወቅ... እግዚአብሔር ማን እንደሆነና በቃሉ ምን እንደሚል ለማወቅ የጠለቀ ፍላጎት ። በተጨማሪም መንፈሳዊ ጨቅላነት ላይ አለመጣበቅን ያመለክታል ።

**ራስን መግዛት** (self control ) : የበሰለ እምነት ማረጋገጫ ነው።
እግዚአብሔርን ስንታመን ፣ የሚለውን ስናውቅ ፣ ማድረግ ከማይገቡን ነገሮች ስንታቀብ የገዛ እኔነት ይኖረናል ።
በሩጫ ልምምድ ላይ እየሰሩ እንዳሉ ፡ ትኩረታቸውንና ሀይላቸውን ልምምዳቸው ላይ ብቻ እንደሚያደርጉ አትሌቶች የሚል አረዳድ አለው።

**መፅናት** ( perseverance ) : የህይወታችን ውጤቶች ከፍላጎቶቻችን ጋር ባይመሳሰሉ እና ባይገጥሙ እንኳን እግዚአብሔርን በማመን ለመቀጠል ያለንን ፈቃደኝነት (willingness ) ያሳያል ።

ራስን መግዛት እና መፅናት እጅ ለእጅ ሲሄዱ የሀጢያት ፈተና እና መከራ ሲመጣ ትክክለኛ የሆነውን ወደማድረግ እንድንሄድ ያግዘናል ።
እነዚህ ሁሉ ባህሪያት ተቀናብረው እግዚአብሔርን ወደ መምሰል ያሳድጉናል።
ኢየሱስ እግዚአብሔርን በመምሰል ፍና ወጊ ሆኖ ምሳሌን ትቶልን ሄዷል።
ኢየሱስን ስንከተል ህይወታችን የእግዚአብሔርን መገኘት እየተለማመደ ይመጣል።

**እግዚአብሔርን መምሰል** (Godliness ) : በእያንዳንዱ የህይወታችን ጉዳይ ላይ እግዚአብሔርን መረዳት ማለት ነው። ጌታ ኢየሱስ በእያንዳንዱ ደቂቃ በምድር ቆይታው የኖረው ህይወት ነው። እውነተኛ መንፈሳነትን አመልካች ነው ። ሐዋርያው ጳውሎስ ለመንፈሳዊ ልጁ ጢሞቴዎስ አፅንኦት የሰጠበት ጉዳይ ነው።

**“ነገር ግን ለዚህ ዓለም ከሚመችና የአሮጊቶችን ሴቶች ጨዋታ ከሚመስለው ተረት ራቅ። እግዚአብሔርን ለመምሰል ግን ራስህን አስለምድ።”**
**— 1ኛ ጢሞቴዎስ 4፥7**

**የወንድማማች መዋደድ** ( brotherly affection or Philadelphia ) : ከራስ ተኮር እና እኔነት የወጣ ራስን ለሌላው መስዋዕት አድርጎ ማቅረብን የሚያመለክት ነው።

**ፍቅር** : የነገር ሁሉ ማሰሪያ እና ፍፃሜ ነው። የመዳናችን እውነት በአምላካዊ ፍቅር መወደዳችን ነው።

በእነዚህ ባህሪያት ማደግ እና መጨመር ያለው ፋይዳ ; ፍሬያማ ህይወት ፣ ሰራተኝነት ያለበት ክርስትና ፣ ሩቅ ተመልካችነት እንዲሁም የደህንነትን ክቡርነት መረዳት ናቸው።

ስለዚህም መጠራታችንንና መመረጣችንን ለማፅናት መትጋት አለብን ፤ በእነዚህ ሁሉ ማደግ እና መጨመር በሙላት በሚመጣው የእግዚአብሔር መንግስት ያለ ሀፍረት በከበረ እምነት መግባት ይሆንልናል ።

እነዚህን ሁሉ አለማፍራት የማይቻልባቸው ምክንያቶች ብዙ ናቸው። አንድም ከላይ በጴጥሮስ መልዕክት እንደተገለፀው የመለኮቱ ሀይል በእኛ ውስጥ ይህን የማድረግ ብቃት እና አቅም አለው። የእግዚአብሔር ከሁሉ የላቀው የሀይሉ ታላቅነት ሰማይን እና ምድርን ሲፈጥር ወይም የኤርትራን ባህር ለሁለት ከፍሎ የእስራኤልን ልጆች በደረቅ ምድር ሲያሻግር ሳይሆን እኛን ከሀጢአት ባርነት ወደ ፅድቅ ወራሽነት ሲያመጣን እንደሆነ መፅሐፍ ይነግረናል።

ሌላው ደግሞ ከምንጩ ጋር የተጣበቀ ማንኛውም ነገር የምንጩን አይነት ባህሪ ይገልጣል ወይም ያፈራል። ውሃ ዳር የተተከለ ዛፍ የማፍራቱ ሁኔታ የሚወሰነው ከአጠገቡ በሚያገኘው ወሃ ነው። ጌታ ኢየሱስ የሁሉ ነገር ምንጭ መሆኑን ለማሳየት እራሱን በወይን ግንድ መስሏል።

**“እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል።”**

**— ዮሐንስ 15፥5**

ቅርንጫፍ በግንዱ ላይ እስካለ ድረስ ማፍራቱ የግድ ነው። ምክንያቱም እንዲያፈራ ሊረዳው የሚችለው ነገር ሁሉ ከዛፉ ተፈቅዶለታል። በዛፉ ውስጥ የሚያልፈው ሁሉ በቅርጫፍ ውስጥ ያልፋል። እኛም አስተማማኝ የምናፈራበት ምንጫችን ኢየሱስ ነው። በእርሱ በኖርን መጠን የእግዚአብሔር ህይወት በህይወታችን እየተገለጠ ይመጣል። በኢየሱስ መኖር ማለት የእርሱን ቃል በእምነት በምድር ላይ መኖር ማለት ነው።

**ዮሐንስ 15**

**7 በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል።**

**8 ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከበራል።**

በዚህ ቃል መኖር ፍሬ እንድናፈራ ያደርገናል። በህይወት ፍሬ መታየት ደግሞ እግዚአብሔር አብን ያስከብረዋል። የኢየሱስ የምድር የቤት ስራው የአብን ፈቃድ አድርጎ መመለስ ነበር። እርሱን በሚገባ ተወጥቶ ወደ አባቱ ተመልሷል። የእኛም የህይወት ጥሪ የኢየሱስን ህይወት ኖሮ አብን አስከብሮ ማለፍ ነው። ሲፅፉት ቀላል ነው ፤ ሲኖር ደግሞ ከባድ። ነገር ግን ፍፁም በተሰጠ ህይወት ወደዛ ማደግ እንደሚቻል መፅሐፍ ቅዱሳችን የሚነግረን እውነታ ነው።

# ከመሄዳችን በፊት አንድ ናፍቆት...

እኔ እንደ አንድ ግለሰብ አንድ ቀሪ ዝናብ ጌታችን ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት ይዘንባል ብለው ከሚያምኑት ወገን ነኝ። ይህ ዝናብ የመጨረሻው ዘመን የክብር ዝናብ ነው። ቤተክርስቲያን ኢየሱስን ብቻ የምታደምቅበት ፣ አማኞች እንደገና የህይወት ተሐድሶ የምናገኝበት ፣ የተቀበልነው የመዳን ወንጌል በዓለም ዙሪያ

ሁሉ የሚሰበክበት እና የእያንዳንዱን የዓለም ህዝብ የሚያንኳኳበት ጊዜ ይመጣል። የእግዚአብሔር ክብር የተገለጠ የእግዚአብሔር ህልውና እና መገኘት ነው። ይህ የእግዚአብሔር ክብር ሲገለጥ ስጋ የለበሰ ሁሉ ተመልካች የሚሆኖበት እንጂ ግለሰቦች የሚገኑበት እና የሚደምቁበት አይደለም ።

**"የእግዚአብሔርም ክብር ይገለጣል፥ ሥጋ ለባሹም ሁሉ በአንድነት ያየዋል፥ የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና።"**

**— ኢሳይያስ 40፥5**

የእግዚአብሔር ክብር ሰዎችን የማድመቅ አላማ የለውም ፤ ኖሮትም አያውቅም። ሙሴ በሲና ተራራ ላይ የእግዚአብሔርን ክብር አይቶ በወረደ ጊዜ የእርሱ ፊት እንደበራ አያውቅም ነበር ፤ የእስራኤል ልጆች ናቸው ነግረውት ለፊቱ መሸፈኛ እንዲያደርግ የነገሩት። የእግዚአብሔር ክብር ውስጥ ራሱን ረስቶ ነው የመጣው።

**ዘጸአት 34**

**29 እንዲህም ሆነ፤ ሙሴ ከሲና ተራራ በወረደ ጊዜ ሁለቱ የምስክር ጽላቶች በሙሴ እጅ ነበሩ፤ ሙሴም ከተራራው በወረደ ጊዜ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለ ተነጋገረ የፊቱ ቁርበት እንዳንጸባረቀ አላወቀም ነበር።**

**30 አሮንና የእስራኤልም ልጆች ሁሉ ሙሴን ባዩ ጊዜ፥ እነሆ የፊቱ ቁርበት አንጸባረቀ ወደ እርሱም ይቀርቡ ዘንድ ፈሩ።**

ሲና ተራራ ላይ የተገለጠው የእግዚአብሔር ክብር ዓላማ ፈሪሃ እግዚአብሔርን እና መታዘዝን በእስራኤል ልጆች ዘንድ ማምጣት ነው። በእግዚአብሔር ክብር ወቅት ሙሴም አብሮ ሰጋጅ እና ተንበርካኪ ነው።

**ዘጸአት 34**

**8 ሙሴም ፈጥኖ ወደ መሬት ተጐነበሰና ሰገደ፦**

**9 አቤቱ በፊትህስ ሞገስን አግኝቼ እንደ ሆነ፥ ይህ አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነውና ጌታዬ በመካከላችን ይሂድ፤ ጠማማነታችንንና ኃጢአታችንንም ይቅር በለን፥ ለርስትህም ተቀበለን አለ።**

የእግዚአብሔር ክብር ሲገለጥ የእግዚአብሔር ህዝብ የህይወት ተሐድሶ ይሆንለታል ። የእስራኤል ህዝብ እግዚአብሔርን በበደለ እና ባሳዘነ ጊዜ ተላልፈው ለምርኮ ተሰጥተው ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር በባርነት ሊተዋቸው አልፈቀደም ። እንደገና የመመለስን ዕድል ሰጣቸው ፣ የፈረሰው የሚሰራበትን ዕድል ሰጣቸው። ይህን የህይወት ተሐድሶ ይናፍቁ የነበሩት የመቅደሱ ሰሪ ዕዝራ እና የእስራኤል ቅጥር ጠጋኝ ነህምያ ነበሩ። የሰማይን አምላክ እረፍት ይነሱት ነበር። ምክንያቱም የአባቶቻቸው አምላክ በእነርሱ ዘመን ዙሪያቸው ባሉ አህዛብ ዘንድ መሳለቂያ እንዲሆን ስላልፈቀዱ ነው። ከንጉስ ቤት የተመቻቸ ሙብል እና መጠጥ ይልቅ እራስ ላይ አመድ ነስንሶ እና ልብን አዋርዶ የህይወት ብልሽት ለገጠመው ህዝብ ቀን እና ሌሊት በአምላክ ፊት አልቃሽ መሆንን የተሐድሶው መሪ ነህምያ መረጠ። እግዚአብሔርም ለቤቱ መፍረስ ቅናት ለበላቸው ሲል ተለመናቸው። ህዝቡም ዳግም ተሐድሶን አገኘ።

**“አሁንም ቅሬታ ይተውልን ዘንድ፥ በተቀደሰውም ስፍራው ችንካርን ይሰጠን ዘንድ፥ አምላካችንም ዓይናችንን ያበራ ዘንድ፥ በባርነትም ሳለን ጥቂት የሕይወት መታደስን ይሰጠን ዘንድ ለጥቂት ጊዜ ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ሞገስ ተሰጥቶናል።”**

**— ዕዝራ 9፥8**

የዚህ የእግዚአብሔር ክብር ዓላማ የእግዚአብሔርን አምላክነት በህዝቡ ዘንድ ማሳወቅ ነው። የወደቀ እንዲነሳ ፣ የሳተ እንዲመለስ ፣ የተጣመመ እንዲቃና የሚያደርግ የእግዚአብሔር የክብር ጉብኝት ነው።

**“ሕዝቤ ሆይ፥ መቃብራችሁን በከፈትሁ ጊዜ ከመቃብራችሁም ባወጣኋችሁ ጊዜ፥ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ።”**

**— ሕዝቅኤል 37፥13**

ምክንያቱም እግዚአብሔር በመለኮታዊ ሀይሉ እና ክብሩ አይደራደርም ። ለዚህ ቀናተኛ አምላክ ስለሆነ። ሁሉን አድራጎቱ የሀይሉን ታላቅነት የሚያሳይ በመሆኑ ይህን የሀይል ታላቅነት የሚመጥን አካሄድ ከህዝቡ የሚፈልግ አምላክ ነው። አንድ ወቅት ላይ በዓል እና እግዚአብሔር እያሉ በሁለት ካርድ እየተጫወቱ በሁለት ሀሳብ ሲያነክሱ እንደነበሩት እስራኤላውያን ሙሉ ሁለንተናን በማይሰጥ ህዝብ እና ግለሰብ የሚደሰት አምላክ አይደለም። መንገድን እና አካሄድን እንደ ቃሉ ያደረገን ማንነት ይፈልጋል።

**"እኔ እግዚአብሔር ነኝ ስሜ ይህ ነው፤ ክብሬን ለሌላ፥ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም።"**

**— ኢሳይያስ 42፥8**

መቼስ ጨለማውን መራገም ብቻውን ብርሀን አያመጣም። በማታ ምንም መብራት በሌለበት አስፓልት ላይ የሚራመድ ሰው ጨለማውን ደጋግሞ ቢሳደብ እና ቢራገም ምናልባት የጨለማውን ጥልቀት ለራሱ ያስረዳ ይሆናል እንጂ ብርሀን አያመጣለትም። ብርሀኑን ማሸነፍ የሚችለው የስልኩን መብራት ማብራት ከቻለ ነው። በዘመናችንም በተለይም በቤተክርስቲያን መፅሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ልምምዶች እና አስተምህሮዎች ይስተዋላሉ። ብዙ የቤተክርስቲያንን ክብር ዝቅ የሚያደርጉ እና ቅዱሱን የእግዚአብሔር ስም የሚያቃልሉ ሁነቶች እዚህም እዚያም ይታያሉ። ብዙዎቻችንም አይተናል ፤ ማየት ብቻ አይደለም አማኛ ካልሆኑት ዘንድም የተቀበልነው መጥፎ ምስክርነት ነው። በእርግጥ እግዚአብሔር ለዚህ ነገር በዛች የፍርድ ቀን ይበቀላል። በክቡር ደሙ የገዛትን ቤተክርስቲያን ባረከሰ እና ባቃለለው ላይ የበቀል በትር የማይቀር ነው።

**"እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።"**

**— ራእይ 22፥12**

ከዛ የፍርድ ቀን በፊት ግን ቤተክርስቲያን ዳግም በመንፈስ ቅዱስ ትጎበኛለች። ወንዶችን ፣ ሴቶችን ፣ ሽማግሌዎችን ፣ ወጣቱን በሀይል የሚያስታጥቅ የመንፈስ ቅዱስ ጉብኝት ይኖራል ።

**"ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል፤ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፥ ጐበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፤"**

**— ኢዮኤል 2፥28**

ይህ የመንፈስ ፍሰት ቤተክርስቲያንን ያለ ነቀፋ እና ሀፍረት እንዲሁም የፊት መጨማደድ በክርስቶስ ፊት እንድትቆም የሚያደርጋት ነው። ቸር ያሰንብተን !

"እንግዶች ነን" !!